# 508

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ የጦር ፡ ሠራዊትንና ፡ የክብር ፡ ዘበኛን ፡ የመለማመጃ ፡ ሰልፍ ፡ በጐበኙበት ፡ ጊዜ ፡ ለዝቅተኛ ፡ ሹማምንቶችና ፡ ለተራ ፡ ወታደሮች ፡ ያስነገሩት ፡ የንጉሣዊ ፡ ችሮታ ፡ ትእዛዝና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተነገረ ፡ ቃል ።

ሀ) የንጉሣዊ ፡ ችሮታ ፡ ትእዛዝ ።

ፀዝቅተኛ ፡ ሹማምንቶችና ፡ በተራ ፡ ወታደሮቻችን ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የኑሮ ፡ ችግር ፡ በመረዳት ፡ ይህንኑ ፡ ችግራቸውን ፡ ለማቃለል ፡ በማሰብ ፡

፩ኛ ፡ የነባርነት ፡ ደሞዝ ፡ እንዲጨመርላቸው ።

፪ኛ ፡ የልጅ ፡ አበል ፡ እንዲያገኙ ፡ ፈቅደናል ።

ማናቸውም ፡ ተራ ፡ ወታደርና ፡ ዝቅተኛ ፡ ሹማምንት ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ያለነውር ፡ በቅንነትና ፡ በታዛዥነት ፡ በታማኝነትና ፡ የተሰጠውን ፡ ቃል ፡ በማክበር ፡ ያገለገለ ፡ ሁሉ ፡ በነባርነት ፡ ተመዝግቦ ፡ በልዩ ፡ አስተያየት ፡ ፈቅደን ፡ ለሰጠነው ፡ መብት ፡ ተገቢ ፡ ይሆናል ።

ለአቅመ ፡ አዳም ፡ ያልደረሱና ፡ በወላጆቻቸው ፡ ትከሻ ፡ የሚኖሩ ፡ ልጆች ፡ ያላቸው ፡ ተራ ፡ ወታደሮችና ፡ ዝቅተኛ ፡ ሹማምንቶች ፡ በተጨማሪ ፡ ከፈቀድንላቸው ፡ ደሞዝ ፡ በላይ ፡ በልጆቻቸው ፡ ቊጥር ፡ ልዩ ፡ አበል ፡ በየወሩ ፡ እንዲቀበሉ ፡ አዘንላቸዋል ።

በዚህ ፡ በሰጠነው ፡ ትእዛዝ ፡ ለመጠቀም ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ወታደሮችና ፡ ዝቅተኛ ፡ ሹማምንቶች ፡ የጦር ፡ ሠራዊታችን ፡ ጠቅላይ ፡ መምሪያ ፡ በሚሰጠው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ልጆቻቸውን ፡ ማስመዝገብ ፡ አለባቸው ።

ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ከታኅሣሥ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የጸና ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራበትና ፡ የጦር ፡ ሠራዊታችን ፡ ጠቅላይ ፡ መምሪያ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ደንብ ፡ አዘጋጅቶ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ አዘንላችኋል ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

በምን ፡ ምክንያት ፡ ይኸን ፡ እንዳደረግንላችሁ ፡ በየጊዜው ፡ ማሰባችን ፡ የወታደር ፡ ውለታውንና ፡ ጥቅሙን ፡ በማወቃችን ፡ ነው ።



ይህን ፡ የምናስብላችሁም ፡ ብዙም ፡ ቢሆን ፡ ትንሽም ፡ ቢሆን ፡ የሚፈጸመው ፡ በየጊዜው ፡ መሆኑ ፡ ግዴታ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

የሹማምንትና ፡ የወታደር ፡ የደስታ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ከመንግሥታችን ፡ ሀብት ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ የሚያድግ ፡ ነው ። ባለፈው ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ለሹማምንት ፡ አባል ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡ ሁሉ ፡ የበላይና ፡ የበታች ፡ ማለት ፡ ሹማምንትና ፡ ወታደርም ፡ ተራ ፡ አላቸው ። ይኸውም ፡ ወታደሮች ፡ በትጋታቸው ፡ ሹማምንት ፡ መሆናቸውን ፡ ታውቃላችሁ ።

የጦር ፡ ሹማምንቶችና ፡ ሠራዊት ፡ ማለት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ ፖሊስ ፡ ሁሉም ፡ በስም ፡ ቢከፋፈል ፡ በሥራ ፡ በሞት ፡ ለነፃነት ፡ በቆራጥነት ፡ ለመሞት ፡ እኛም ፡ ጭምር ፡ እኩል ፡ ነን ።

ለማስረጃ ፡ አባቴ ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ ነበሩ ።ላገራቸው ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ደማቸውን ፡ እንዳፈሰሱ ፡ ማነው ፡ ይኸን ፡ የማያውቅ ?

ራሳችንም ፡ ቢሆን ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ከወታደር ፡ ያልተለየ ፡ ሥራ ፡ ሠርተናል ። ስለዚህ ፡ እንደዚሁ ፡ ልጆቻችንም ፡ ዘሮቻችንም ፡ ሁሉ ፡ የወታደርነት ፡ ደም ፡ ያለባቸው ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።

ሹማምንትና ፡ ወታደርን ፡ ጥቅሙን ፡ አውቀን ፡ ነው ፡ ያቋቋምነው ። ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በደሙ ፡ በወታደርነት ፡ ያልተመረዘ ፡ ማን ፡ ይገኛል ? ይኸውም ፡ በአርበኝነትም ፡ ጊዜ ፡ በጦርነትም ፡ ጊዜ ፡ የተመሰከረ ፡ ነው ።

ለዚሁም ፡ መለያ ፡ ወታደርም ፡ ሹማምንትም ፡ ቢሆን ፡ አንዳንድ ፡ ቅሌተኛ ፡ እንደሚገኝበት ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ ለዘር ፡ ይተላለፋል ፡ በጀግንነትና ፡ በወታደርነት ፡ በሚገባ ፡ የሞቱም ፡ ካባት ፡ እየተወረሰ ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ አባቶቻችን ፡ ስማቸውን ፡ እንዳስጠሩ ፡ እንደዚሁ ፡ እናንተም ፡ በተራችሁ ፡ መልካም ፡ ስማችሁን ፡ ለልጆቻችሁ ፡ የምትተው ፡ ናችሁ ።

ሹማምንትና ፡ ወታደር ፡ የሰላም ፡ ጊዜ ፡ ክብራችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አጥር ፡ ለምንላችሁ ፡ ከዚህ ፡ ካደረግንላችሁ ፡ በቀር ፡ ወደፊት ፡ ለሰላማዊውም ፡ ሕዝባችን ፡ ለመላውም ፡ የጦር ፡ ሠራዊታችን ፡ ብዙ ፡ ፕሮግራም ፡ አለን ።

ይኸውም ፡ ስለ ፡ ትምህርቱ ፡ ስለ ፡ ጤናው ፡ ስለ ፡ ኑሮው ፡ ወታደር ፡ ያለበትን ፡ ግዴታና ፡ መሥዋዕትነት ፡ እንዲያስብ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ለኅዙ ፡

እንዳያስብ ፡ በተቻለን ፡ የምንሠራበትን ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ በመጨረሻው ፡ የምንነግራችሁ ፡ የምንጠላውንና ፡ የምንወደውን ፡ ነው ።

ለወታደር ፡ የሚገባው ፡ ለወሬ ፡ መመከት ፡ ታቊኝነት ፡ በነውር ፡ ቦታ ፡ እንዳይገኝ ፡ መጠንቀቅ ፡ ነው ። ቃል ፡ ኪዳናችሁን ፡ አክብራችሁ ፡ ለሞት ፡ ዝግጁ ፡ መሆን ፡ ይህ ፡ ከእናንተ ፡ የምንፈልገው ፡ ነው ።

የምንጠላው ፡ ዲስፕሊንን ፡ አለማክበር ፡ ውስልትናን ፡ ወሬ ፡ ፈጥሮ ፡ ማውራትን ፡ ነው ። ያላችሁበት ፡ ቦታ ፡ የስም ፡ ክብር ፡ ያለበት ፡ ነውና ፡ ክብራችሁን ፡ መጠበቅ ፡ ነው ።

ወደፊት ፡ የምናስብላችሁን ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝር ፡ ሠርቶ ፡ እንድትጠቅሙ ፡ ለማድረግ ፡ ጊዜ ፡ የሚወስድ ፡ ሀብት ፡ የሚጠይቅ ፡ በመሆኑ ፡ ይህንኑ ፡ የሰጠናችሁን ፡ ቃል ፡ ለማክበር ፡ በየጊዜው ፡ የመንግሥቱ ፡ ሀብት ፡ እንደ ፡ እድገቱ ፡ በሚያድግበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ከእናንተው ፡ ማህል ፡ እንዳንድ ፡ ሆነን ፡ የምናስባችሁ ፡ መሆናችንን ፡ እንድታውቁት ፡ ነው ።

---

# 509

የበጌምድርና ፡ የሰሜን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ለማበርከት ፡ አስቦ ፡ በሎንዶን ፡ ኤክስፕሬስ ፡ ኮምፓኒ ፡ ያሠራውን ፡ ልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ በጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ በክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አሥራተ ፡ ካሣ ፡ አማካይነት ፡ ጥቅምት ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ፡ ነገሥትና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ሲያቀርብ ፡ ጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አሥራተ ፡ ካሣና፡ የድርጅቱ ፡ ኮሚቴ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተከበሩ ፡ ደጃዝማች ፡ ገሠሠ ፡ ረታ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አሥራተ ፡ ካሣ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ፳፭ኛው ፡ በዓለ ፡ ንግሥዎ ፡ ለዋለበት ፡ ለዚህ ፡ ዘመን ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የበጌምድርና ፡ የስሜን ፡ ሕዝብዎ ፡ ይህን ፡ መታሰቢያ ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ በሚገኙት ፡ ከየአውራጃው ፡ ተመርጠው ፡ በመጡ ፡ መልክተኞች ፡ አቅርቧል ።

የመልክተኞቹ ፡ መሪና ፡ ሕዝቡም ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ በተለይ ፡ ለቆመው ፡ ኮሚቴ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ አድርጎ ፡ የሾማቸው ፡ ከሕዝቡ ፡ የተላከትን ፡ መልእክት ፡ ይገልጹ ፡ ዘንድ ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ እለምናለሁ ።

* * *



ለ) የተከበሩ ፡ ደጃዝማች ፡ ገሠሠ ፡ ረታ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ።

ግርማዊት ፡ እቴጌ ።

ለደረስንበት ፡ ፳፭ኛ ፡ በዓለ ፡ ንግሥዎ ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ታማኝና ፡ ከልብ ፡ አፍቃሪዎ ፡ የበጌምድር ፡ ሕዝብ ፡ ይህን ፡ የሻማ ፡ መብራት ፡ አቅርቧል ። ይኸውም ፡ ማብሪያ ፡ ሙሉ ፡ ሥራው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለሕዝብዎ ፡ የዋሉትን ፡ ወረታ ፡ በምሳሌ ፡ የሚገልጽ ፡ ሆኖ ፡ የተሰናዳ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ፳፭ ፡ ሻማ ፡ የሚያበራ ፡ መሆኑ ፡ ፳፭ቱ ፡ ዓመታት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥትዎ ፡ አገርዎ ፡ የጥበብ ፡ ብርሃን ፡ ያየችበት ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ ፳፭ቱ ፡ ማብሪያዎች ፡ ሳይለያዩ ፡ ባንድነት ፡ ለማብራት ፡ መቻሉ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የዘረጉት ፡ የሥልጣኔ ፡ ትምህርት ፡ ብርሃን ፡ ለመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባንድነት ፡ ያለአድልዎ ፡ እኩል ፡ ያበራ ፡ ለመሆኑ ፡ ምሳሌ ፡ ከወርቅና ፡ ከብር ፡ የሀገርዎና ፡ የሕዝብዎን ፡ ልማትና ፡ እድገት ፡ ብርታትና ፡ ጥንታዊ ፡ ኑዋሪነት ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ። ዛሬ ፡ እኛ ፡ ያየነውን ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራና ፡ ያገኘነውን ፡ የኑሮ ፡ መሻሻል ፡ ዘመን ፡ አባቶቻችን ፡ ሳይመኙት ፡ አልቀሩም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ማህሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጊዜሁ ፡ እንደተባለ ፡ አባቶቻችን ፡ ተመኝተው ፡ ያላገኙት ፡ የተድላ ፡ ጊዜ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ለኛ ፡ ስለተሰጠ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ለሚያዩ ፡ ዓይን ፡ ሁሉ ፡ ምስጋና ፡ ይገባዋል ። ከ፲ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. በኢትዮጵያ ፡ ነግሠው ፡ ከነበሩት ፡ ፪፻፳፭ ፡ ነገሥታት ፡ ውስጥ ፡ ከሥራ ፡ ታሪክዎ ፡ የምናወዳድረው ፡ ከዕድልዎ ፡ የምናመዛዝነው ፡ አላገኘንም ።

ምክንያቱም ፡ ለሰው ፡ ብሎ ፡ ነፍሱን ፡ በፈቃዱ ፡ መሥዋዕት ፡ ያደረገ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ በቀር ፡ እስካሁን ፡ ያልተገኘ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ ሕዝቅያስን ፡ አባቶችህ ፡ ያከማቹት ፡ በቤትህ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ተማርኮ ፡ ባቢሎን ፡ ይሄዳል ፡ ልጆችህም ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ግምብ ፡ ጠባቂ ፡ ይሆናሉ ፡ ቢለው ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡ መልካም ፡ ነው ፡ በዘመኔ ፡ ጽድቅና ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ለራሱ ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ አሰበ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ የግል ፡ ምኞት ፡ የዕለት ፡ ደስታ ፡ የሚሹ ፡ ባለመሆንዎ ፡ ለዛሬውና ፡ ለሚመጣው ፡ ትውልድ ፡

ጥቅም ፡ የሚሆን ፡ መሠረታዊ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ ስላየን ፡ ከአለፉት ፡ ነገሥ ታት ፡ ሁሉ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የለዎም ፡ ስንል ፡ ተከራካሪ ፡ አይገኝም ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ **ለዕብራውያን ፡ ሰዎች ፡ ሲጽፍ ፡ ሁሉን ፡ ልናገር ፡ ብሻ ፡ ጊዜ ፡** ያጥረኛል ፡ እንዳለ ፡ እንደዚሁም ፡ እኛ ፡ ከአልጋ ፡ ወራሽነትዎ ፡ ጀምረው ፡ ለመላ ፡ ሕዝብዎ ፡ ያደረጉለትን ፡ ውለታ ፡ ዘርዝረን ፡ ለመናገር ፡ ብናስብ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጅብን ፡ ስለሆነ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አድርገዋል ፡ ይህም ፡ እያንዳንዱ ፡ ቢጻፍ ፡ ዓለም ፡ እንኳ ፡ ባልቻለውም ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ ንግግራችንን ፡ እናሳጥራለን ።

ይህ ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ የሆነው ፡ መታሰቢያ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ በሚታይበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በምሉ ፡ ልቦና ፡ የሚያፈቅርዎ ፡ ታማኝ ፡ ሕዝ ብዎ ፡ መሆኑን ፡ እንዲያስታውሱለት ፡ ከሕዝብዎ ፡ የቀረበ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ላደረጉልን ፡ ወረታዎ ፡ የምንሰጠዎ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ማና ቀር ፡ **መታመን ፡ ታዞ ፡ መሥዋዕት ፡ መሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ።**

ግርማዊነትዎ ፡ ከኛ ፡ የሚፈልገው ፡ ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ **ቅዱስ ፡ ፍቅር ፡ ንጹሕ ፡ አገልግሎት ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ካቀረብነው ፡ ብዙ ፡** ብልጫ ፡ ያለው ፡ በረከት ፡ አቅርበን ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ከመስጠት ፡ በቀር ፡ መቀበልን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የማይፈቅዱ ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ።

**በበጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የሚገኘው ፡ ሕዝብዎ ፡ ከዘር ፡ ተያ** ይዞ ፡ ለመጣው ፡ የትውልድ ፡ ዙፋንዎ ፡ ያልተቋረጠ ፡ በፍቅርና ፡ በታማ ኝነት ፡ የተመሠረተ ፡ ግንኙነት ፡ ስላለው ፡ ኑዋሪ ፡ ኩራቱ ፡ ነው ።

ይህ ፡ የታወቀ ፡ መንፈስ ፡ ብርቱ ፡ ጠንቃቃ ፡ የሆነ ፡ ሕዝብዎ ፡ ታሪክ ፡ ምስክሩ ፡ ሆኖ ፡ እንደሚያስረዳለት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነጻነትና ፡ ሃይ **ማኖት ፡ ላይ ፡ ዐምፀውና ፡ ተነሥተው ፡ የነበሩትን ፡ እንደ ፡ አንዳንድ ፡ ዓላውያን ፡ ያሉትን ፡ ጠላቶች ፡ ሁሉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቶቹን ፡ እየተከተለ ፡** ስደትና ፡ መከራ ፡ እየተቀበለ ፡ የመጨረሻውን ፡ ድል ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ **ጦር ፡ ግምባር ፡ እየተሰለፈ ፡ በበጌምድር ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ድልን ፡ ያገኘ ፡** ነው ።

አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ግፈኛው ፡ ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረ ፡ ጊዜ ፡ **መላው ፡ የበጌምድር ፡ ሕዝብ ፡ አርበኛ ፡ ሁኖ ፡ ጠላትን ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡** ሥልጣኑና ፡ ግዛቱ ፡ እንዳይስፋ ፡ አድርጎ ፡ ተጋድሎ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማና ፡ መንግሥት ፡ በሀገሩ ፡ ላይ ፡ ሳይታጠፍ ፡ በካርቱም ፡



በኩል ፡ የግርማዊነትዎ ፡ መምጣት ፡ ሲበሥር ፡ ቀዳሚ ፡ ሆኖ ፡ የቀረበና ፡ የተቀበለ ፡ በመጨረሻውም ፡ የጠላት ፡ መደምሰስና ፡ ድል ፡ መገኘት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ከሰጡት ፡ መሪ ፡ ከተወደደ ፡ ልጅዎ ፡ ከልዑል ፡ የኢትዮ ጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ጋር ፡ ተሰልፎ ፡ ጐንደር ፡ ላይ ፡ የመሸ ገውን ፡ ጠላት ፡ በማስለቀቅ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ያስገኘ ፡ ነው ።

እንደዚህ ፡ ያለ ፡ የታመነ ፡ ጠባይ ፡ ያለን ፡ ሕዝቦችዎ ፡ ንጉሣችንን ፡ አፍቃሪ ፡ አገራችንን ፡ አክባሪ ፡ ስለሆን ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ለግር ማዊነትዎና ፡ ለወራሾችዎ ፡ የምንገዛ ፡ ታማኝና ፡ ታዛዥ ፡ አገልጋይ ፡ መሆ ናችንን ፡ ስንገልጽ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ እየተሰማን ፡ ነው ።

ታላቅ ፡ ታምራት ፡ ለታየበትና ፡ ለተሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መታ ሰቢያ ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ ማቆም ፡ ጉልህ ፡ ማስረጃ ፡ ዋና ፡ ምስክር ፡ የማ **ይደመሰስ ፡ ከትውልድ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ የሚደርስ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡** ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ ሥርዓት ፡ በመሆኑ ፡ እነሆ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ይህን ፡ መታሰቢያ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ከልብ ፡ የደስታ ችን ፡ መግለጫ ፡ ሆኖ ፡ አቅርበናልና ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ አግኝቶ ፡ የዘወትር ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆነን ፡ ዘንድ ፡ ከዙፋንዎ ፡ ሥር ፡ ወድ ቀን ፡ እንለምናለን ።

* * *

ሐ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ሁላችሁም ፡ እንደምታውቁት ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኛ ፡ ያደረገው ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። በንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ **ደስታና ፡ ክብር ፡ ሲሰጠን ፡ ዘመንም ፡ አብዝቶልናል ። በቸርነቱ ፡ ነፃነታ** ችንን ፡ መልሶ ፡ እኛም ፡ ተመልሰን ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ ዘመነ ፡ መንግ ሥት ፡ ማብቃቱ ፡ በሱ ፡ ጥበብ ፡ የሚመረመር ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ የሚያው ቀው ፡ አይደለም ።

**የበጌምድር ፡ ሕዝብ ፡ እኛን ፡ የሚወደንና ፡ የሚያውቀን ፡ ንጉሠ ፡** ነገሥትና ፡ አልጋ ፡ ወራሽም ፡ ከመሆናችን ፡ በፊት ፡ ስለሆነ ፡ የሚያስብ ልንና ፡ የምናስብለት ፡ ነበር ። ይህንንም ፡ አሁን ፡ በሕይወት ፡ ያላችሁት ፡ **ታውቁታላችሁ ። የበጌምድር ፡ ሕዝብ ፡ ውለታ ፡ መላሽ ፡ መሆኑ ፡ የታ**

ወቀ : ነው ።

አሁንም : ይህንን : ከልብ : አስባችሁ : ያቀረባችሁልንን : መታሰቢያ : የምንቀበላችሁ : በደስታ : ነው ። ይህም : መታሰቢያ : ለባለውለተኛነታችሁ : ምስክር : ሆኖ : ይኖራል ።

ከዚህ : ከወርቅ : ከተሠራው : መታሰቢያ : የበለጠ : ደማችሁን : በማፍሰስ : ያደረጋችሁት : አገልግሎትና : የከፈላችሁት : ውለታ : የበለጠ : ነው ። እግዚአብሔር : ይስጣችሁ ።

---

# 501

የኢጣሊያ : ሬፑብሊክ : መንግሥት : ልዩ : መልክተኛና : ባለሙሉ : ሥልጣን : አምባሳደር : ክቡር : ሙሴ : አልቤርቶ : ቤርዮ : ጥቅምት : ፲፫ : ቀን : ፲፱፻፵፰ : ዓ. ም. በ፫ : ሰዓት : በገነተ : ልዑል : ቤተ : መንግሥት : የሹመት : ደብዳቤያቸውን : ለግርማዊ : ንጉሠ : ነገሥት : ሲያቀርቡ : ላደረጉት : ንግግር : ከግርማዊነታቸው : የተሰጠ : መልስ ።

ሀ) የግርማዊ : ንጉሠ : ነገሥት : ንግግር ።

ክቡር አምባሳደር ።

በቤተ : መንግሥታችን : ዘንድ : የክቡር : የኢጣሊያ : ሬፑብሊክ : መንግሥት : ፕሬዚዳንት : ልዩ : መልክተኛና : ባለሙሉ : ሥልጣን : አምባሳደር : ሆነው : የተሾሙበትን : ደብዳቤ : ከእጅዎ : ስንቀበል : ከእርስዎ : በፊት : ለነበሩት : የተከበሩ : አምባሳደር : የነበረንን : መልካም : አስተያየትና : ግምት : ሳንገልጸው : አናልፍም ።

ክቡርነትዎ : በንግግርዎ : እንደገለጹት : ተቀዳሚው : የነበሩት : ሚቼ : አምባሳደር : ታኮሊ : ለአገራቸው : አገልግሎት : ሕይወታቸውን : ሰጥተዋል ።

እንደዚሁም : በኢትዮጵያና : በኢጣሊያን : መካከል : ላሉት : መልካም : ግንኙነት : መስፋፋት : ብዙ : ይደክሙ : እንደ : ነበሩ : በሥራ : ታይቷል ።

ክቡርነትዎን : በቤተ : መንግሥታችን : ስንቀበል : ደስ : እያለን : ለተላኩበት : ተግባር : መልካም : አፈጻጸም : በሚያደርጉት : ሁሉ : በጎ : አስተያየታችንን : እንደሚያገኙ : ልናረጋግጥልዎ : እንወዳለን ። በሚኒስ



ትሮቻችን : ላይ : የሕዝባችንም : እርዳታ : አይጓደልብዎም ።

ባሁኑ : ጊዜያት : በሁለቱም : አገሮች : መካከል : ካሉት : ጉዳዮች : ታላቅ : ቁም : ነገር : የምንሰጣቸው : ዐይነተኛና : አስቸኳይ : የሆኑ : ባጭር : ጊዜ : ውስጥ : መልካም : ፍጻሜ : እንዲያገኙና : ፍጻሜያቸውም : የሁለቱን : አገሮች : ኅብረት : የሚያረጋግጥ : መሠረቱ : እየጸና : የሚሄድ፡ እንዲሆን : ተስፋ : እናደርጋለን ። ለኛና : ለቤተ : ሰቦቻችን : ስለገለጹት : መልካም : ምኞት : ምስጋናችንን : እያቀረብን : የመጡበት : ከፍ : ያለ : መልክት : እንዲቃናልዎ : ምኞታችንን : እንገልጣለን ።

---

# 511

የጃፓን : ንጉሠ : ነገሥት : መንግሥት : ልዩ : መልክተኛና : ባለሙሉ : ሥልጣን : ሚኒስትር : ክቡር : ሚስተር : ሺጂሩ : ዩሳኖ : ጥቅምት : ፲፯ : ቀን : ፲፱፻፵፰ : ዓ. ም. በ፫ : ሰዓት : በገነተ : ልዑል : ቤተ : መንግሥት : የሹመት : ደብዳቤያቸውን : ለግርማዊ : ንጉሠ : ነገሥት : ሲያቀርቡ : የተናገሩት : ቃልና : ከግርማዊነታቸው : የተሰጠ : መልስ ።

ሀ) የክቡር : ሚኒስትሩ : ንግግር ።

ከግርማዊነትዎ : ዘንድ : የጃፓን : ልዩ : መልክተኛና : ባለሙሉ : ሥልጣን : ሚኒስትር : ሆኜ : ከግርማዊ : የጃፓን : ንጉሠ : ነገሥት : የተሾምኩበትን : የክብር : ደብዳቤ : ከፍ : ካለው : ከግርማዊነትዎ : እጅ : ሳቀርብ፡ ለኔ : ከፍ : ያለ : ክብሬ : ነው ።

በጃፓንና : በኢትዮጵያ : መካከል : ከዚህ : በፊት : የነበረውን : ግንኙነት : እንደገና : ለማስፋፋትና : ለመመሥረት : እንዳገለግል : ለዚህ : ከፍ : ያለ : ሥራ : በመመረጤ : የተሰማኝን : ጥልቅ : ደስታ : ለመግለጽ : እደፍራለሁ ።

በዓለም : ላይ : የደረሱት : አሠቃቂ : ጊዜያቶች : የተሳሰሩትን : የሁለታችንን : ወዳጅነት : ለጥቂት : ጊዜያቶች : ያህል : ቢያቋርጡትም : ይህ፡ ከፍተኛ : ግምትና : የልብ : የወንድማማችነት : በሁለቱ : ሕዝቦቻችን : መካከል : በየልቦናቸው : ውስጥ : ተቀርጾ : መኖሩን : አልዘነጋውም ።

ግርማዊነትዎ : ኢትዮጵያ : ወደፊት : እንድትራመድ : ላደረጉትና : ላከናወኑት : የሚያስደንቅ : ሥራ : የጃፓን : ሕዝብ : ከልቡ : የቀረጸውን፡

አድናቆት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እንድገልጽ ፡ የተላክሁትን ፡ መልክት ፡ ለመ ናገር ፡ ይፈቀድልኝ ።

ከብዙ ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣው ፡ የግር ማዊነትዎ ፡ ንጉሣዊ ፡ ትውልድ ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንዳኰራት ፡ እንዲሁም ፡ በጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ኵራትን ፡ መሥርቷል ። ስለዚህ ፡ የሁለቱ ፡ ሕዝቦ ቻችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ተባብሮ ፡ ለመሥራትና ፡ ለሚሆን ውም ፡ የጋራ ፡ መግባባት ፡ ጽኑ ፡ መሠረትን ፡ ይሰጠዋል ። አገሮቻቸው ፡ እንደገና ፡ በበለጠ ፡ እንዲስፋፉና ፡ እንዲሁም ፡ የተወደደ ፡ ባህላቸውንም ፡ በሙሉ ፡ በመጠበቅ ፡ ለዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ አሠራር ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ ሕዝቦቻችን ፡ በሙሉ ፡ ይደክማሉ ።

የሁለቱ ፡ ሕዝቦች ፡ ተባብሮ ፡ መሥራት ፡ ያላቸውን ፡ የጋራ ፡ አሳ ብና ፡ ተመሳሳይ ፡ ጠባይ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ምክንያትና ፡ ለሕዝብ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ከመርዳት ፡ እንደማያቋርጡ ፡ ተረድቼዋለሁ ። በያገሩ ፡ በሁለቱ ፡ ሕዝቦቻችን ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ እንዲስፋፉና ፡ እንዲጠነክሩ፡ ለማከናወን ፡ በተጣለብኝ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ቸል ፡ የምልበት ፡ አሳብ ፡ የለም ። ይህን ፡ ከፍተኛ ፡ ሥራ ፡ በማከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥትዎና ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እምነትና ፡ መልካም፡ ድጋፍ ፡ እንደማይለየኝ ፡ ባለ ፡ ተስፋ ፡ መሆኔን ፡ ለመናገር ፡ እደፍራለሁ ።

ለግርማዊነትዎና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ጸጋ ፡ እንዲሁም ፡ ለኢት ዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ልማት ፡ ያላቸውን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እንድገልጽ ፡ ግር ማዊ ፡ የጃፓን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ያዘዙኝን ፡ መልክት ፡ እንዳቀርብ ፡ የግር ማዊነትዎን ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ እለምናለሁ ።

❊ ❊ ❊

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ሚኒስትር ።

በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የጃፓን ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትዎ ፡ የተ ሾሙበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ከእጅዎ ፡ ስንቀበል ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ከጃፓን ፡ ጋራ ፡ የነበረን ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ግንኙነት ፡ እንደገና ፡ በመ ከፈቱ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ክቡርነትዎ ፡ ባደረጉት ፡ ንግግር ፡ የኢት



ዮጵያና ፡ የጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የቆየው፡ ንጉሣዊ ፡ ዘር ፡ ጠቃሚያቸው ፡ መሆኑን ፡ በሚገባ ፡ ጠቅሰውታል ። እነ ዚህ ፡ ሁለት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገሮች ፡ የራሳቸውን ፡ ጥንታዊ ፡ ልማ ድና ፡ ጽኑ ፡ እምነት ፡ ሳይለቁ ፡ መልካምና ፡ ጠቃሚ ፡ በሆኑት ፡ ዘመናዊ ዘዴዎች ፡ ሲጠቀሙ ፡ ይታያሉ ።

በሁለቱም ፡ ታላላቅ ፡ ክፍለ ፡ ዓለሞች ፡ ምሥራቃዊ ፡ ጫፍ ፡ የሚገ ኙት ፡ ሁለቱ ፡ ጥንታውያን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛቶች ፡ ወደፊት ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ የሚግባቡባቸውንና ፡ የሚተባበሩባቸውን ፡ ብዙ ፡ መንገዶች ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚችሉ ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

በኛ ፡ አስተዳደር ፡ ሥር ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ የሚሠራባቸው ፡ የኢትዮ ጵያ ፡ የጥንት ፡ ወደቦች ፡ መከፈት ፡ በመርከብ ፡ ንግድ ፡ ረገድ ፡ ከረጅም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ከሆነችው ፡ ከጃፓን ፡ ጋር ፡ በበለጠ ፡ አኳ ኋን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለማስፋፋት ፡ የሚያስችል ፡ እንዲሆን ፡ ተስፋ ፡ እና ደርጋለን ።

ክቡርነትዎ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥትዎ ፡ ትእዛዝ ፡ የተላኩበትን ፡ ሥራዎን፡ ለመፈጸም ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ የኛና ፡ የሚኒስትሮቻችን ፡ እር ዳታና ፡ ኅብረት ፡ እንደማይጓደልብዎ ፡ እናረጋግጥልዎታለን ።

ይህንን ፡ መልካም ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ለግርማዊ ፡ የጃፓን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰባቸው ፡ የወዳጅነት ፡ ሰላ ምታችንን ፡ እንዲያቀርቡልንና ፡ እንደዚሁም ፡ ለጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ልማትና፡ ደኅንነት ፡ ያለንን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እንዲገልጹልን ፡ እንጠይቅዎታ ለን ።

---

# 512

የኤርትራ ፡ ሕዝብ ፡ ፳፭ኛውን ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ምክንያት ፡ ማድረግ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለማበርከት ፡ ያዘጋጀውን ፡ መታሰቢያ ፡ የኤርትራ ፡ ቺፍ ፡ ኤግዚክ ቲፍ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አስፍሐ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ጥቅምት ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ለግ ርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አስፍሐ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊት ፡ እቴጌ ።

ኢትዮጵያን ፡ እንዲመሩ ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመርጠው ፡ ባባቶችዎ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ከተቀመጡ ፡ ጀምሮ ፡ ስላገርዎና ፡ ስለ ፡ ሕዝብዎ፡ ደኅንነትና ፡ ሥልጣኔ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የውስጥና ፡ የውጭ ፡ ለመለወጥ ፡ የፈጸሟቸው ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ የሆኑት ፡ ተግባሮች ፡ በታሪካችንና ፡ ባገራቱም ፡ መልክ ፡ ላይ ፡ ተቀርጸው ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚመሰክሩ ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ በችሎታቸውና ፡ በአደራረሳቸው ፡ የታወቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሳይቀሩ ፡ ደክመውበታል ። የበለጠ ፡ መግለጫ ፡ ላልሰጥ ፡ ወርቃዊ ፡ ጊዜዎን ፡ ለማባከን ፡ አልሞክርምና ፡ ቸርነትዎ ፡ እንዲሆንልኝ ፡ በፍጹም ፡ ትሕትና ፡ እለምናለሁ ።

ከታላላቆቹ ፡ ተግባሮችዎ ፡ አንዱ ፡ የኤርትራን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መመለስ ፡ ስለሆነ ፡ ይኸውና ፡ ዛሬ ፡ ይህች ፡ ፍጹም ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ የሆነች ፡ ግዛትዎ ፡ ከ፷፪ ፡ ዓመት ፡ የጠላት ፡ ጭቆናና ፡ የባርነት ፡ ኑሮ ፡ በኋላ ፡ ከኢትዮጵያዊው ፡ ቤተ ፡ ሰቧ ፡ ተቀላቅላ ፡ ነፃነትን ፡ ተጎናጽፋ ፡ የወላጅ ፡ አባቷን ፡ የዘውድ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ለማክበር ፡ በመታደሏ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የሰማያዊ ፡ አምላክ ፡ ቸርነት ፡ እንደሌለ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ የመንግሥቱን ፡ ዛብ ፡ ጨብጠው ፡ ኢትዮጵያን ፡ መምራት ፡ ከጀመሩበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ፡ በ፲ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የኤርትራን ፡ ወደ ፡ እናት ፡ አገርዋ ፡ መመለስ ፡ ለሥራዎ ፡ ቀዳሚ ፡ ያደረጉት ፡ መሆኑን ፡ በማወቅ ፡ ተራው ፡ ሕዝብ ፡ ሳይቀር ፡ "ምነው ፡ ቀደም ፡ ባለ ፡ ያንተ ፡ መወለድ ፡ አሥመራ ፡ ምጥዋ ፡ ሳይሄድ ፡" እያለ ፡ የትካዜ ፡ ስሜቱን ፡ ሲገልጽ ፡ ቀጥሎም ፡ "ጠቅል ፡ ጠቀለለ ፡ ከፈረስ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ . . . አሥመራን ፡ ምጽዋን ፡ ሊያመጣ" እየተባለ ፡ ሕዝባዊ ፡ ትንቢቱን ፡ ሲናገር ፡ የሕዝብ ፡ ድምፅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ሆኖ ፡ የአንዲት ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፡ ሳይኖርዎት ፡ ተወዳዳሪ ፡ የለውም ፡ ተብሎ ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ በተገመተው ፡ አስተዋይነትዎና ፡ መሪነትዎ ፡ ይህን ፡ ታላቁን ፡ ታሪክ ፡ ለመፈጸም ፡ ቻሉ ። የሕይወታችንን ፡ መቆየት ፡ የምንመኘው ፡ የተበታተኑትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦች ፡ ለመሰብሰብ ፡ ነው ፡ የሚለውም ፡ ንጉሣዊ ፡ ቃልዎ ፡ ይህ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ ፡ አገኘ ።



ስለዚህ ፡ የኤርትራ ፡ ሕዝብ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ የነፃነቱን ፡ ጌታ ፡ የዘውድ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ የሚያከብረው ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ የውለታ ፡ መላሽነት ፡ ስሜትም ፡ ጭምር ፡ ነው ። እንደተመለከትኩት ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ፡ ያለው ፡ የጋለ ፡ መንፈስና ፡ ናፍቆት ፡ ልክ ፡ ታቦትን ፡ ለማንገሥ ፡ እንደሚሰናዳ ፡ እንጂ ፡ ዓለማዊውን ፡ በዓል ፡ ለማክበር ፡ የሚዘወተረው ፡ ልማዳዊ ፡ አደራረግ ፡ አይደለም ። ባገሩ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የሥነ ፡ በዓሉ ፡ ስሜትና፡ ድርጅት ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ሲሆን ፡ ተወዳጁ ፡ የኤርትራ ፡ ሕዝብዎ ፡ ለዚህች ፡ ለታላቅ ፡ ቀን ፡ የመልካም ፡ ምኞቱ ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የላከውን ፡ ይህን ፡ የታማኝነት ፡ የደስታና ፡ የፍቅር ፡ አምኃ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ በሕዝቡ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ልመናዬን ፡ አቀርባለሁ ።

በዚሁም ፡ ለአምኃ ፡ በቀረበው ፡ ምስል ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በጠቅል ፡ ፈረስዎ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ በአሥመራ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ሲያመሩ ፡ ያመለክታል ። ይኸውም ፡ ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ የመከራና ፡ የባርነት ፡ የመርዝ ፡ መተላለፊያና ፡ የመውረሪያ ፡ ጦር ፡ መከማቻ ፡ ደጃፍ ፡ ሆኖ ፡ የተፈጥሮ ፡ ተግባሩ ፡ ተበላሽቶ ፡ የቆየው ፡ የኤርትራ ፡ ባሕር ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ድካምና ፡ ከአምላክ ፡ ባገኙት ፡ ከፍተኛ ፡ ግርማ ፡ የሀብትና፡ የነፃነት ፡ የብልጽግናና ፡ የሥልጣኔ ፡ ደጃፍ ፡ ሆኖ፡ ወደተፈጠረበት ፡ መልክና ፡ ተግባር ፡ መለወጡን ፡ ለማስገንዘብ ፡ ነው ።

በኤርትራ ፡ የመሬት ፡ አቀማመጥ ፡ መጠን ፡ የተሠራው ፡ ጂዖግራፊ፡ የአውራጃዎቿን ፡ የከተማዎቿን ፡ የደሴቶቿን ፡ የወደቦቿን ፡ ስም ፡ ከመጥቀሱ ፡ በላይ ፡ በየጊዜው ፡ ለመውረር ፡ የተነሡትን ፡ ጠላቶች ፡ ለመመለስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መሬት ፡ አናስነካም ፡ በማለት ፡ ጀግኖች ፡ አባቶችዎና ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ደማቸው ፡ የፈሰሰባቸውን ፡ አጥንታቸው ፡ የተከሰከሰባቸውን ፡ የጦር ፡ ሜዳዎች ፡ ያመለክታል ።

ሓያ ፡ አምስቱ ፡ ኮከቦች ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ፳፭ኛውን ፡ የዘውድ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ የሚያስታውሱ ፡ ናቸው ።

ግርማዊ ሆይ ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ያቀረቡለት ፡ አምኃ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ለአምላክነቱ ፡ የሚበቃ ፡ ባይሆን ፡

የሕሊናቸውን ፡ እምነት ፡ አይቶ ፡ እንደተቀበላቸው ፡ ሁሉ ፡ ግርማዊነትዎም ፡ በሕሊና ፡ የሚያምንዎት ፡ የሚተማመንብዎት ፡ የሚያፈቅርዎት ፡ የኤርትራ ፡ ሕዝብ ፡ የላከውን ፡ አምኃ ፡ በመቀበል ፡ እንዲያስደስቱት ፡ በፍጹም ፡ ትሕትና ፡ እየለመንሁ ፡ ዛሬ ፡ የብር ፡ ኢዮቤልዩን ፡ ለማየት ፡ በቸርነቱ ፡ ያበቃን ፡ አምላክ ፡ በሰላምና ፡ በደስታ ፡ ጠብቆ ፡ የወርቅ ፡ ኢዮቤልዩዎንም ፡ ለማክበር ፡ እንዲያስችለን ፡ በኤርትራ ፡ ሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆኜ፡ የማቀርበውን ፡ ልባዊ ፡ ምኞት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ እጅ ፡ ነስቼ ፡ እለምናለሁ ።

❊ ❊ ❊

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

የኤርትራ ፡ ሕዝብ ፡ በጠለቀ ፡ አሳብ ፡ አስቦ ፡ ይህንን ፡ ሳለንም ፡ በአጠገባችን ፡ የምናየውን ፡ ካለፍንም ፡ በኋላ ፡ ለኤርትራም ፡ ሕዝብ ፡ ለኛም ፡ ለራሳችን ፡ መታሰቢያ ፡ የሚሆነውን ፡ በማቅረቡ ፡ መንፈሱ ፡ ያልገፋው ፡ አፉ ፡ አይናገርም ፡ ሥራውም ፡ አይተካከልም ፡ መንፈሳችሁ ፡ ከልብ ፡ ያሰባችሁበት ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳናልና ፡ ይህን ፡ በማድረጋችሁ ፡ ከልብ ፡ እናመሰግናችኋለን ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ የኤርትራ ፡ ሕዝብ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ሳለም ፡ ቢሆን፡ ከጠላትም ፡ ነፃ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ የማይረሳ ፡ ከዚህ ፡ ከመታሰቢያ ፡ ግምት ፡ በሌለው ፡ ዋጋ ፡ ደሙን ፡ እንዳፈሰሰልን ፡ ወደእናት ፡ አገሩ ፡ ለመቀላቀል ፡ እንደኋኋ ፡ ደማቸውንም ፡ ያላፈሰሱት ፡ በመንፈሳቸውና ፡ በሐሳባቸው ፡ ሲኋጉልን ፡ እንደኖሩ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አንረሳምና ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ዘወትር ፡ አስታዋሽ ፡ ይሆነናል ። ከልብ ፡ ባደረጋችሁት ፡ ከልብ ፡ እናመሰግናችኋለን ። እግዚአብሔር ፡ ይስጥልን ።

---

# 513

የትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ ያዘጋጀውን ፡ የወርቅ ፡ ሐውልትና ፡ የወርቅ ፡ ጋሻ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. በጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ በልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ መንገሻ ፡ አማካይነት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያበረክት ፡ ክቡር ፡ የአቡስም ፡ ንብረ ፡ እድ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።



ሀ) የክቡር ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የእግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ ምንም ፡ ለፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የማያቋርጥ ፡ ቢሆን ፡ ዕድል ፡ ገጥሞን ፡ በየጊዜው ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ በተለይ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ የቸርነቱ ፡ ሥራዎች ፡ በየዕለቱና ፡ በየዓመቱ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸውና ፡ ለመቍጠር ፡ ባንችል ፡ በትዕግሥት ፡ ወስነን ፡ ሥራህ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ከልባችን ፡ እናመሰግነዋለን ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

"ስም ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ይመራል ፡" ተብሎ ፡ እንደተጻፈ ፡ ቀዳማዊ ፡ ሲባሉ ፡ ለስምዎ ፡ ብቻ ፡ መስሎ ፡ ታይቶ ፡ ነበረ ። አሁን ፡ ግን ፡ በሥራና ፡ በታሪክም ፡ ቀዳማዊ ፡ ሆኖ ፡ አገኘነው ።

ካሁን ፡ ቀደም ፡ የነበሩት ፡ አባቶችዎ ፡ ነገሥታት ፡ ይህን ፡ የኢዮቤልዩ ፡ በዓል ፡ አክብረውት ፡ አያውቁም ፡ ነበረ ። ዘመነ ፡ መንግሥትዎ ፡ ፳፭ ፡ ሆኖ ፡ በማክበርዎ ፡ ቀዳማዊ ፡ ሆኑልን ።

ኢዮቤል ፡ ማለት ፡ በሱባዔ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ። ከግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ቀጥሎ ፡ ዕለቱን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መባል ፡ የሚገባዎ ፡ ሲሆን ፡ ታግሠው ፡ እስከ ፡ ጥቅምት ፡ ድረስ ፡ ፯ ፡ ወር ፡ ነው ። ፯ቱ ፡ የወር ፡ ሱባዔ ፡ ሆነዋል ። በዕለት ፡ የኢዮቤል ፡ አቈጣጠርም ፡ ፵፱ ፡ ሱባዔ ፡ ነው ። በነዚህ ፡ ሱባዔዎች ፡ ሁሉ ፡ ታዝኖባቸውና ፡ ተመጽውቶባቸው ፡ ሱባዔዎች ፡ ሲፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ ሁሉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተባሉ ። ጠላትም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ዘውድ ፡ በኀዘንና ፡ በፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ ነውና ፡ ከጠላት ፡ እጅ ፡ ሳይወድቅ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሳይለይ ፡ በክብር ፡ ተመልሶ ፡ እነሆ ፡ ፳፭ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ተብሎ ፡ የበዓሉን፡ አርእስት ፡ ለማግኘት ፡ ችሏል ። እንደ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በስደት ፡ ሄደው ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ሳይመለሱ ፡ የቀሩት ፡ የብዙ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። እስካሁን ፡ ዘውዶችና ፡ ባለ ፡ ዘውዶቹ ፡ በባዕድ ፡ ሀገር ፡ ይገኛሉ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ግን ፡ የአጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘውድና ፡ የአጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ሰይፍ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ከተወሰዱ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በዕድልዎና ፡ በብርታትዎ ፡ ተመልሰዋል ።

ይህ ፡ ዘውድ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የታሪኳ ፡ ማኀልመሻና ፡ የጠላቶቿ ፡ ድል ፡ መንሻ ፡ ምልክት ፡ ነው ። ሀብቱ ፡ መዊዕም ፡ የተሰጠው ፡ የዘውዶች ፡ ዘውድ ፡ ነው ።

ተዋግቶ ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ ለሁሉም ፡ ይሰጠዋል ፡ ሳይዋጉ ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ተአምራት ፡ ተቆጥሮ ፡ ለዚህ ፡ ባለ ፡ ዕድል ፡ ዘውድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የተሰጠው ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ ሲነሣ ፡ በኀይልና ፡ የብዙዎቹን ፡ ደም ፡ በማፍሰስ ፡ ዛሬ ፡ ኤርትራ ፡ የምትባለውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰሜን ፡ ብሔረ ፡ ሐማሴንን ፡ ይዟት ፡ ሲኖር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ወረራት ። ከ፷ ፡ ዓመት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወረራ ፡ በኋላ ፡ ይህችው ፡ ብሔረ ፡ ሐማሴን ፡ ጦርነት ፡ ሳይደረግባትና ፡ የሰው ፡ ደም ፡ ሳይፈስባት ፡ እነሆ ፡ በ፳ ፡ ዘመን ፡ አንዲት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሆናለች ። በደቡብም ፡ በኩል ፡ ሄዶ ፡ ከነበረው ፡ ከሶማሌ ፡ ምድር ፡ ተመልሶዋል ።

ይህ ፡ ዘውድ ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ ተንሥኦ ፡ ሰሜን ፡ ወነዓ ፡ ደቡብ ፡ ብሎ ፡ ጠርቶ ፡ ያቀረበ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ አለ ?

ከዚህስ ፡ የተሻለ ፡ ምን ፡ ዕድል ፡ አለ ?

ስለዚህ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ሲባል ፡ በኵረ ፡ በዓላት ፡ የበዓላት ፡ መጀመሪያ ፡ የበዓላት ፡ በኵር ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ የትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሹማምንትና ፡ ሠራተኞች ፡ በልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ ሰብሳቢነት ፡ ለዚህ ፡ ለ፵፫ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲሆን ፡ የአኵስም ፡ ነገሥታት ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ ባቆሙት ፡ ሐውልት ፡ አምሳል ፡ ተቀርጾ ፡ በወርቅ ፡ ሰንሰለት ፡ በተሰናሰሉ ፡ በ፬ ፡ በወርቅ ፡ አንበሳዎች ፡ የተከበበ ፡ ይህን ፡ የወርቅ ፡ ሐውልትና ፡ የወርቅ ፡ ጋሻ ፡ ከወርቅ ፡ ይልቅ ፡ ለሚወደደው ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እናቀርባለን ።

ታሪካዊውን ፡ ሐውልት ፡ ተዋግቶና ፡ ሳይዋጋ ፡ ድል ፡ ለነሣና ፡ ለሚነሣ ፡ ለባለታሪኩ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ስናበረክት ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ከፍተኛ ፡ ዕድል ፡ ስላጋጠመን ፡ ዕድላችንን ፡ እናደንቃለን ።

ይህ ፡ ያቀርብነው ፡ የወርቅ ፡ ሐውልት ፡ ቅጽል ፡ የሌለበት ፡ ሥረ ፡



ወጥ ፡ ነው ። የግርማዊነትዎ ፡ ትውልድ ፡ ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ድረስ ፡ ቅጽል ፡ የሌለበት ፡ አማናዊው ፡ ሥረ ፡ ወጥ ፡ ነው ። በአኵስም ፡ ሐውልት ፡ አምሳል ፡ አስቀርጸን ፡ ያቀረብነው ፡ ይህ ፡ መታሰቢያ ፡ ቦታው ፡ ስለቀረበንና ፡ ስላየነው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለትውልድዎ ፡ መሠረት ፡ ማስረጃ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘነው ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ የሰው ፡ ዘርና ፡ የነገሥታት ፡ ዙፋን ፡ መገኛ ፡ ይህ ፡ ሐውልት ፡ ከቆመበት ፡ መዲና ፡ አኵስም ፡ የተገኘና ፡ የበቀለ ፡ ነው ።

የዚህም ፡ ማስረጃ ፡ ኖባና ፡ ሶባ ፡ አብርሃ ፡ ወአጽብሐ ፡ የተገኙበት ፡ ከዚሁ ፡ ሆኖ ፡ ፩ኛ ፡ ከተማቸው ፡ በአኵስም ፡ ሲሆን ፡ ፪ኛው ፡ ከተማቸው ፡ በኤረር ፡ ነበረ ። ከዚያ ፡ አያይዞ ፡ የመንግሥት ፡ ዘር ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተዘርቶና ፡ ሥልጣኑን ፡ ዘርግቶ ፡ ሳያቋርጥ ፡ እስከ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የደረሰ ፡ ነውና ፡ ቅጽል ፡ የሌለው ፡ ሥረ ፡ ወጥ ፡ ዘርዐ ፡ መንግሥት ፡ ያልንበት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

የዚህ ፡ ሐውልት ፡ ከአንድ ፡ ደንጊያ ፡ ተቀርጾ ፡ ሳይለወጥ ፡ ዕገሌ ፡ ቅጽል ፡ ሳይኖርበት ፡ ለታሪክ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንግዳ ፡ ቢመለከቱት ፡ የማይሰለች ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ ያባቶችዎ ፡ የጀብዱ ፡ ሥራቸውና ፡ የዕውቀትርቀታቸው ፡ ምስክር ፡ ስለሆነ ፡ ዛሬ ፡ ላለው ፡ ትውልድ ፡ ኩራት ፡ ይሰጠዋል ።

አማናዊ ፡ ከሱ ፡ የተገኘልን ፡ የትውልዳቸውም ፡ ሐውልትነት ፡ ከቆመብት ፡ መንግሥት ፡ ሳይነቃነቅ ፡ እነሆ ፡ ከዚህ ፡ ደርሶ ፡ የዘውድን ፡ በዓል ፡ ሲያከብር ፡ ኩራቱ ፡ ከላይ ፡ ለጠቀስናቸው ፡ ለአባቶችዎና ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ለሚተኩ ፡ ደቂቀ ፡ መንግሥት ፡ በጠቅላላውም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ይህ ፡ ያቀረብነው ፡ የወርቅ ፡ ጦርና ፡ ሰይፍ ፡ ያለበት ፡ የወርቅ ፡ ጋሻ ፡ የትግሬ ፡ ሕዝብ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ በር ፡ የቀረበው ፡ ስለሆነ ፡ የውጭ ፡ ጠላት ፡ በመጣ ፡ ቍጥር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ደሙንና ፡ የጠላቱን ፡ ደም ፡ እንዳፈሰሰበትና ፡ ጨዋነቱን ፡ ሳይዘነጋ ፡ እየተከላከለ ፡ የኖረ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ በአጼ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ቱርክ ፡ በጠላትነት ፡ ሲመጣ ፡ ደሙን ፡ ስለ ፡ አገሩ ፡ ነፃነት ፡ ቀዳሚ ፡ ሆኖ ፡ ያፈሰሰ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

፪ኛም ፡ በአጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ቱርክ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ ሲመጣ ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ከመረብ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ጉራዕ ፡ ድረስ፡ በየጊዜው ፡ የተዋጋበትና ፡ ድል ፡ እየነሣ ፡ የቈራጥነቱን ፡ መንፈስ ፡ የገለጸበት ፡ እውነተኛ ፡ ጀግና ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

አሽከሮቻቸው ፡ እነራስ ፡ አሉላም ፡ በኤርትራ ፡ ምዕራብ ፡ መታሕት ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሰብዶራት ፡ ድረስ ፡ እየተከላከሉ ፡ ጠላትን ፡ ድል ፡ የሚነሡበት ፡ የጀግኖች ፡ እናት ፡ ሀገር ፡ ናት ።

፫ኛ ፡ ኢጣልያ ፡ መጀመሪያ ፡ ሲመጣ ፡ ሰሐጢ ፡ በዶጋሊ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ጠላትን ፡ ወግቶ ፡ የመለሰ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

ደርቡሽ ፡ የጐንደርና ፡ የአካባቢዎቿን ፡ ሕዝብ ፡ ባረደ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ባነደደ ፡ ጊዜ ፡ ለሕዝባቸውና ፡ ለሃይማኖታቸው ፡ ሲሉ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ሰማዕት ፡ የሰማዕታት ፡ መጨረሻ ፡ አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ መተማ ፡ ወርደው ፡ ሊቀ ፡ ሰማዕታት ፡ ሲሆኑ ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞቱት ፡ የዚሁ ፡ ሀገር ፡ መኳንንትና ፡ ሠራዊት ፡ ከቍጥር ፡ የበዙ ፡ ናቸው ። ምስክራቸውም ፡ ሞታቸውና ፡ ታሪካቸው ፡ ነው ።

ከአድዋ ፡ ጦርነትም ፡ አስቀድሞ ፡ ኢጣልያ ፡ በግፍ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ቀዳሚ ፡ ሆኖ ፡ ከኰዓቲት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ እንደርታ ፡ ድረስ ፡ በራስ ፡ መንገሻ ፡ አዝማችነት ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ከወጋው ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ወገን ፡ ስለወረረ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ የራሶች ፡ ራስ ፡ መኰንንን ፡ የጦር ፡ አዝማች ፡ አድርገው ፡ ሲዋጉ ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ በተወለደበት ፡ ሀገር ፡ በጀግንነት ፡ ተዋግቷል ።

እንደዚሁ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከኢጣልያ ፡ ጋራ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ በልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ አዝማችነት ፡ የጦር ፡ ሰፈር ፡ ሆኖ ፡ ሲዋጋና ፡ ሲያዋጋ ፡ የመጀመሪያው ፡ የጦር ፡ ወላፈን ፡ ሳይጐፈንነው ፡ ፯ ፡ ወር ፡ ምሉ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ሥቃይ ፡ በመቀበልና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታማኝ ፡ በመሆን ፡ የተፈተነ ፡ ነው ።

ጋሻ ፡ የያዘ ፡ ጀግና ፡ በጋሻ ፡ እንደሚከላከልና ፡ የተወረወረውን ፡ ጦር ፡ ጋሻው ፡ እንዲጋርድለት ፡ ጋሻውንም ፡ ሳይወጋ ፡ ባለጋሻውን ፡ እንደማይወጋ ፡ የትግሬ ፡ ሕዝብም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጋሻ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ጠላት ፡ በመጣ ፡ ቍጥር ፡ የሚከላከልና ፡ ጦር ፡ የማይጠመርረው ፡ ፊቱንም ፡ ከመከራ ፡ የማይመልስ ፡ የተሳለ ፡ የኢትዮጵያ ፡ በረኛ ፡ ለመሆኑ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።



በጋሻው ፡ ላይ ፡ ጦርና ፡ ሰይፍ ፡ ያለበት ፡ መሆኑም ፡ መከላከል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ጋሻ ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ጦርና ፡ ሰይፍ ፡ ይዞ ፡ የተሰለፈ ፡ ሀገር ፡ ነው ።

በጦርነቱም ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ እጆቹ ፡ ቀኞች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ግራ፡ እጅ ፡ የለውም ። ስለዚህ ፡ በጋሻው ፡ ላይ ፡ ሰይፍና ፡ ጦር ፡ መታየቱ ለትግሬ ፡ ሕዝብ ፡ የቅርብ ፡ ዘመዶቹና ፡ የመከራ ፡ ጊዜም ፡ ጓደኞቹ ፡ ስለሆኑ ፡ እነዚህ ፡ መሣርያዎች ፡ በጋሻው ፡ ላይ ፡ ተሠርተው ፡ ይታያሉ ።

ዛሬም ፡ የትግሬ ፡ ሕዝብ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ለጋስነት ፡ በየዐይነቱ ፡ የተደረገለት ፡ ችሮታ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ፍቅር ፡ በልቡ ፡ ውስጥ ፡ እንዳቀረበው ፡ ሐውልት ፡ ተቀርጾ ፡ እንደ ፡ ጋሻው ፡ ተነግቦ ፡ ይገኛል ።

ይኸውም ፡ የታማኝነቱና ፡ የፍቅሩ ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲሆን ፡ በታማኙ ፡ በትግሬ ፡ ሕዝብዎ ፡ ስም ፡ ሆነን ፡ እነዚህን ፡ መታሰቢያዎች ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እናቀርባለን ።

በሌዋውያን ፡ በ፳፭ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ኢዮቤልን ፡ የደስታ ፡ ዓመት ፡ ናትና ፡ የተቀደሰች ፡ ትሁንላችሁ ፡ እንዳለ ፡ ይህች ፡ የ፳፭ኛ ፡ የዘውድ ፡ ዓውደ ፡ ዓመታችን ፡ የተቀደሰች ፡ ትሁንልን ።

እግዚአብሔር ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ በመስጠት ፡ ዕድሜዎን ፡ አርዝሞና ፡ ሕይወትዎን ፡ አድሶ ፡ ለ፷ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ እንዲያደርስልን ፡ እንለምናለን ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡
ኢትዮጵያ ፡ ለዘለዓለም ፡ በነፃነት ፡ ትኑር ።

❊ ❊ ❊

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

የትግሬ ፡ ሕዝብ ፡ በልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ አማካይነት ፡ የአኵስምን፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ ጨምሮ ፡ ያቀረበልንን ፡ ይህን ፡ መታሰቢያ ፡ ከልብ ፡ በደስታ ፡ የምንቀበለው ፡ ነው ።

የትግሬ ፡ ሕዝብ ፡ ታሪኩን ፡ ቢናገሩለት ፡ የሚያኮራ ፡ ነው ። ለአገሩ ፡ ታማኝነት ፡ ላገሩ ፡ መሞት ፡ ወሰንም ፡ እንዳይተላለፍ ፡ ለመከላከል ፡ የደከመበት ፡ በማንም ፡ አንደበትና ፡ በማንም ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የሚገኝለት ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ለመላው ፡ አገራቸው ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ የተከበረና ፡ የተደነቀ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ አንገታቸውን ፡ ለሰይፍ ፡ ሰጥተው ፡ ወሰን ፡ አስከብረው ፡ የሞቱ ፡ በመሆናቸው ፡ አኩሪነታቸው ፡ ለትግሬ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

ይህንም ፡ ከልባችን ፡ የምናደንቀው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሄደውም ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ የዐጽማቸው ፡ የትም ፡ ወድቆ ፡ መቅረት ፡ ሲያሳዝን ፡ በመኖሩ ፡ ወደ፡ ሱዳን ፡ በሄድን ፡ ጊዜ ፡ ይህንኑ ፡ ለመመርመርና ፡ ለመድረስ ፡ ዐጽማቸውንም ፡ አንድም ፡ ስንጣሪ ፡ አጥንት ፡ እንኳ ፡ ብትሆን ፡ አምጥተን ፡ አገራቸው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ለማሳረፍ ፡ ሞክረን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ ነገር፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ አይሆንምና ፡ ዘመን ፡ የበዛበት ፡ ነገር ፡ ስለ ሆነ ፡ ለማግኘት ፡ ሳንችል ፡ ቀረን ። እንደዚህ ፡ ሆነው ፡ ላገራቸው ፡ ለሞቱት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አባቴ ፡ በዳግማዊ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ተልከው፡ ሄደው ፡ ሳይወለዱ ፡ እንደተወለዱ ፡ ሆነው ፡ የወለዷቸውም ፡ ልጃችሁ ፡ የሞቱትም ፡ በሞት ፡ እንደ ፡ አባት ፡ ሆነው ፡ የወለዷቸው ፡ ይኸው ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ ተርፈው ፡ ይገኛሉ ።

ስለዚህ ፡ ትግሬ ፡ የወለድንበትም ፡ የተወለድንበትም ፡ ታማኞችንም ፡ በረኞችንም ፡ ብለን ፡ የምንጠራውና ፡ የምንቊጥረው ፡ ሕዝብ ፡ ነው ። አሁንም ፡ ይህንን ፡ አሳብ ፡ አስቦ ፡ እንኳን ፡ ሳለን ፡ ከሕይወታችንም ፡ በኋላ ፡ ዘወትር ፡ የሚታይ ፡ መታሰቢያ ፡ በማምጣቱ ፡ ከልብ ፡ ደስ ፡ አሰኝቶናል ። እግዚአብሔር ፡ ይስጣችሁ ።

---



# 514

የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ያዘጋጁትን ፡ መታሰቢያ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ.ም. ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ዘውዴ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተነገረ ፡ አጭር ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ሀ) የአቶ ፡ መኰንን ፡ ዘውዴ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ስለ ፡ አገርዎና ፡ ስለሕዝቦችዎ ፡ ያደረጉልንና ፡ የሚያደርጉልን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሰብአዊ ፡ ርኅራኄና ፡ ቸርነት ፡ በኛ ፡ አንደበት ፡ ሊነገር ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሆነ ፡ አነጋገር ፡ ከቶ ፡ ልናገኝለት ፡ አልቻልንም ።

ሆኖም ፡ ሰው ፡ ልባዊ ፡ ስሜቱና ፡ ፍቅሩ ፡ ሊከፈልለት ፡ የሚችል ፡ ዐቅሙ ፡ በሚፈቅድለት ፡ መጠን ፡ በሚያደርገውና ፡ ባደረገው ፡ ሥራ ፡ ነው ።

በግርማዊነትዎ ፡ ዙፋን ፡ ሥር ፡ የቀረብን ፡ አገልጋዮችዎ ፡ በያንዳንዳችን ፡ ሕይወታዊ ፡ ኑሮአችን ፡ ላይ ፡ የሚደርስብንን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕመምና ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ችግር ፡ ለመከላከል ፡ የመረዳዳትና ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ማኅበር ፡ አቋቁመን ፡ ማኅበራዊ ፡ በሆነ ፡ ኑሮ ፡ መረዳዳት ፡ ከጀመርን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፡ የገናናው ፡ ግርማዊነትዎንም ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ በየዓመቱ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ እናከብራለን ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ለአገር ፡ የሚጠቅም ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ማኅበራችን ፡ በመጀመሪያ ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ እጁን ፡ ይዘረጋል ። ለዚሁም ፡ ማስረጃ ፡ አድርገን ፡ የምንገልጸው ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ገዳማት ፡ እርዳታ ፡ በተጠየቀበት ፡ ጊዜ ፡ የመጀመሪያውን ፡ እርዳታ ፡ ያበረከተ ፡ ይህ ፡ ማኅበር ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የተወዳጁ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ማኅበራችን ፡ በየዓመቱ ፡ የሚያከብር ፡ ቢሆንም ፡ የዛሬው ፡ ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ከሌላው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በበለጠ ፡ የሚከበርበት ፡ ታላቅ፡ በዓል ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ በተለመደው ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩ ፡ በዓ

ሉን ፡ ቢያከብር ፡ የአየርና ፡ የምድር ፡ የቅዝቃዜ ፡ መለኪያ ፡ በወርቅ ፡ ከተሠራ ፡ ሰዓት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ በትሕትና ፡ እነሆ ፡ ያበረክታል ።

የዚህም ፡ ምሳሌ ፡ በአየርም ፡ በባሕርም ፡ በየብስም ፡ ጠባቂያችን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ስለሆነ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓልዎ ፡ ያደረሰዎ ፡ አምላክ ፡ እንደዚሁም ፡ በየዓመቱ ፡ እንዲያደርስልን ፡ እንለምናለን ።

❊ ❊ ❊

ለ) የግርማዊነታቸው ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ንግግራችሁም ፡ ስጦታችሁም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው ። በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተደጋግፎ ፡ መኖር ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ በበለጠ ፡ እያጠነከራችሁ ፡ እንድታስፋፉት ፡ ያስፈልጋል ። እግዚአብሔር ፡ ይስጥልን ።

---

# 515

ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ኀሙስ ፡ ከጧቱ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ስለ ፡ ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በመናገሻ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጽር ፡ ውስጥ ፡ በተደረገው ፡ የሬፍሬሽመንት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ እጅግ ፡ የተከበሩ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ውቤ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ውቤ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የግርማዊነትዎ ፡ ሐያ ፡ አምስተኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ በሚከበርበት ፡ በዚህች ፡ በታሪካዊ ፡ ቀን ፡ በሚወድዎ ፡ ሕዝብዎ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ እንኳን ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዚህ ፡ አደረሰዎ ፡ ለማለት ፡ የመጀመሪያው ፡ ዕድል ፡ ስለ ፡ ተሰጠኝ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብርና ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ይሰማኛል ።

የዛሬ ፡ ሐያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ባባቶችዎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ለመቀመጥ ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በተመረጡ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብዎ ፡ ያስተዳደርን ፡ ደንብና ፡ ሥርዓት ፡ ያወቀም ፡



ቢሆን ፡ በበለጠ ፡ በመንግሥትዎ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይና ፡ እረዳት ፡ እንዲሆን ፡ በማለት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የሕዝብዎን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፓርላማን ፡ በገዛ ፡ ፈቃድዎ ፡ አቋቋሙ ።

ይህ ፡ በነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ ምሳሌ ፡ የሌለው ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ስም ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥፍራ ፡ አስገኝቷል ።

ባለፉት ፡ ሐያ ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የፈጸሟቸውን ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ለመዘርዘር ፡ የጊዜው ፡ ማጠር ፡ አይፈቅድም ።

ኢትዮጵያ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የምትገኝበት ፡ አስደናቂ ፡ የሆነ ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ደግሞም ፡ በዓለም ፡ መንግሥታት ፡ መካከል ፡ የያዘችው ፡ የክብር ፡ ቦታ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ድካም ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ የሰጠ ፡ ለመሆኑ ፡ በቂ ፡ ምስክር ፡ ነው ።

ዓለም ፡ በታላቅ ፡ ችግርና ፡ በጦር ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ በምትኖርበት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ያህል ፡ አስተዋይና ፡ አዋቂ ፡ መሪ ፡ በማግኘቷ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከተሰጧት ፡ ዕድሎቿ ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ነው ።

ግርማዊነትዎ ፡ ረጅም ፡ ዕድሜና ፡ መልካም ፡ ጤና ፡ አግኝተው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ትልቅነትና ፡ ለሕዝብዎ ፡ ብልጽግና ፡ ያቀዱትን ፡ ሁሉ ፡ የሥልጣኔ ፡ ፕሮግራም ፡ ለመፈጸም ፡ አምላካችን ፡ በቸርነቱ ፡ እንዲያበቃዎ ፡ ያለኝን ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ ምኞት ፡ እገልጻለሁ ።

መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታማኝነት ፡ በበለጠ ፡ የደስታው ፡ ተካፋይ ፡ መሆኑ ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡
ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተወላጆች ፡
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

❊ ❊ ❊

ለ) ከግርማዊ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ይህ ፡ አሁን ፡ ያለንበት ፡ አደባባይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አደባባይ ፡ ነው ፤ ለሰ

ው ፡ ምስጋና ፡ አይገባውም ፡ ምስጋና ፡ የሚገባው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ምስጋና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሁን ። በመማክርቶቹ ፡ ስምና ፡ በሕዝብ ፡ ስም ፡ ሆነህ ፡ ያቀረብክልን ፡ ቃል ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ እና መሰግናለን ።

---

# 516

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በተከበረበት ፡ በጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. በፓርላሜንት ፡ የተናገሩት ፡ የዙፋን ፡ ቃል ።

በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ በሦስት ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ያልተደረገውን ፡ በፈቃዳችን ፡ ለተወደደው ፡ ሕዝባችን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከሰጠነው ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ፳፬ ፡ ዓመት ፡ ሆነ ።

በሰጠነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሰበብ ፡ ሕዝባችን ፡ ያደረገውን ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃና ፡ የደረሰበትን ፡ የዕውቀት ፡ ደረጃ ፡ በመመልከት ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ማሻሻልና ፡ ለሚመጣው ፡ ዘመን ፡ በቂ ፡ መሪነት ፡ የሚኖረው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ማደራጀት ፡ ማስፈለጉን ፡ ተረድተን ፡ ዛሬ ፡ የ፳፭ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓላችን ፡ በሚከበርበት ፡ ቀን ፡ አውጀን ፡ ስንሰጥ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ዘመናዊ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሁላችንም ፡ ናት ፡ የሚያሰኘው ፡ አስተዳደር ፡ የተመሠረተው ፡ የዛሬ ፡ ፳፬ ፡ ዓመት ፡ ይጠቅማል ፡ ብለን ፡ ያደራጀነውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሰጠን ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

በ፳፬ቱ ፡ ዓመታት ውስጥ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የደረሱት ፡ ከባድ ፡ ፈተናዎች ፡ መለዋወጥ ፡ መሠረቱን ፡ ሊያናውጡት ፡ ስላልቻሉ ፡ ቀዋሚ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራታችን ፡ የታመነ ፡ ማስረጃ ፡ ሆኖአል ።

በጠላት ፡ በተወረርንበት ፡ ዘመንና ፡ ነጻነታችንን ፡ በክብር ፡ ካስመለስን ፡ በኋላም ፡ በዚሁ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተመሠረተው ፡ አስተዳደር ፡ ኃይሉ ፡ ሳይቀነስ ፡ መሠረቱ ፡ ሳይፋለስ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሲሠራ ፡



ቆይቷል ፤ ስለዚህ ፡ ከ፳፬ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ተገቢነቱንና ፡ ጠቃሚነቱን ፡ አውቀን ፡ የሰጠነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አገልግሎቱን ፡ አስረድቷል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ ሕዝባችን ፡ የደረሰበትን ፡ ደረጃ ፡ በመመልከትና ፡ ወደፊትም ፡ በበለጠ ፡ እርምጃ ፡ ወደከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ በማወቅ ፡ የቆየውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሰፊ ፡ አስተያየት ፡ ማሻሻል ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አገኘነው ።

ዛሬ ፡ በዚህ ፡ ከምትገኙት ፡ ታማኝ ፡ ዜጎቻችን ፡ መካከል ፡ የዛሬ ፡ ፳፬ ፡ ዓመት ፡ የነበሩትን ፡ ሁኔታዎች ፡ በማስታወስ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በነበረውና ፡ ዛሬ ፡ ባለው ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ለማመዛዘን ፡ ትችላላችሁ ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ምኞታችንና ፡ አሳባችን ፡ ለሕዝባችን ፡ ደኅንነትና ፡ እድገት ፡ ስለሆነ ፡ አገራችን ፡ በኤኮኖሚ ፡ ሀብት ፡ በዕውቀት ፡ ረገድ ፡ እየደረጀ ፡ እንዲሄድና ፡ የሕዝቡም ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ እንዲሻሻል ፡ ማድረግ ፡ የማያቋርጥ ፡ ተግባራችን ፡ ነው ።

በእነዚሁ ፡ የማሻሻል ፡ እርምጃዎች ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከቀድሞው ፡ የሚበዛ ፡ ተወላጅ ፡ ሕዝብ ፡ አስፍራለች ። እንደዚሁም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ ከቀድሞው ፡ ዘመን ፡ ዛሬ ፡ በብዛት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በንግድና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ደርጅተው ፡ ይታያሉ ።

የሕዝቡን ፡ ቍጥር ፡ እየበዛ ፡ እንዲሄድ ፡ ካደረጉት ፡ ምክንያቶች ፡ ከ፳፬ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ያልነበሩ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲደራጁ ፡ ያስደረግናቸው ፡ ዘመናዊ ፡ ሥራዎች ፡ ይገኛሉ ። ለምሳሌ ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የነበሩት ፡ ሆስፒታሎች ፡ ወይም ፡ የሕክምና ፡ መስጫ ፡ ቦታዎች ፡ ከ፵፰ ፡ የማይበልጡ ፡ ነበሩ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ ከ፪፻፵ ፡ የማያንሱ ፡ ሆስፒታሎችና ፡ የሕክምና ፡ ቤቶች ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተዘርግተው ፡ አገልግሎታቸውንና ፡ እርዳታቸውን ፡ በየሥፍራው ፡ ለሕዝባችን ፡ እንዲያበረክቱ ፡ ተደርጓል ።

ጤናን ፡ በመጠበቅ ፡ ሞት ፡ እንዲቀነስና ፡ ዘር ፡ እንዲበዛ ፡ በመሆኑ ፡ ሕፃናቶች ፡ ከመልካም ፡ ጤና ፡ ጋራ ፡ ተገኝተው ፡ በብዛት ፡ በትምህርት ፡ እንዲጎለምሱ ፡ ለማድረግ ፡ ተቻለ ።

በመናገሻ ፡ ከተማችን ፡ ቀድሞ ፡ ያልነበሩ ፡ ለሕዝብ ፡ ምቾት ፡ የተ

ሠሩ ፡ ዘመናዊ ፡ ሥራዎች ፡ ስለሚገኙ ፡ የሕዝቡም ፡ ቍጥር ፡ እያደገ ፡ ስለሄደ ፡ የከተማውን ፡ ስፋት ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ከእጥፍ ፡ እንዲበልጥ ፡ አድርጎታል ።

ይህን ፡ ምኞት ፡ ሁሉ ፡ በመናገሻ ፡ ከተማችን ፡ ብቻ ፡ ሳንወስን ፡ በሌሎቹም ፡ ከተሞቻችን ፡ እንዲዳረስ ፡ ተዘርምሯል ። ይኸውም ፡ ለአገራችን ፡ ልማትና ፡ እድገት ፡ ካቀድነው ፡ ፕሮግራም ፡ አንዱ ፡ ነው ።

የአንድ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ እርስ ፡ በርሱም ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ ዓለም ፡ ጋራም ፡ ቢሆን ፡ ለመቀራረብና ፡ ለመተዋወቅ ፡ ሀብቱንም ፡ ለመለዋወጥ ፡ የሚችለው ፡ መገናኛ ፡ሲኖረው ፡ ነው ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ ከሚሊዮን ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ካሬ ፡ በላይ ፡ ያላት ፡ አገራችን ፡ የሚገባትን ፡ መገናኛ ፡ እንድታገኝ ፡ ሳንደክምበት ፡ አልቀረንም ።

ከዓለም ፡ ጋራ ፡ የሚያገናኘን ፡ የራዲዮ ፡ ስልክ ፡ አቋቁመናል ። በመንገድም ፡ ረገድ ፡ ከአፍሪቃ ፡ ምሥራቅ ፡ ጠረፍ ፡ ከሚገኙት ፡ ከማናቸውም ፡ አገር ፡ የተሻሉ ፡ የውስጥ ፡ መገናኛዎች ፡ አሉ ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በተለይ ፡ አስበንበት ፡ ተቋቁሞ ፡ በመልካም ፡ አኳኋን ፡ ሥራውን ፡ሲያከናውን ፡ የሚታይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዓየር ፡ መንገድ፡ ይገኛል ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከማናቸውም ፡ ከሌሎቹ ፡ የዓለም ፡ ከተሞች ፡ በሳምንት ፡ ሳይሆን ፡ በሰዓት ፡ በሚቈጠር ፡ ርቀት ፡ ላይ ፡ እንድትገኝ ፡ ስላደረጋት ፡ ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አገራችንን ፡ ያለችግር ፡ ለመጐብኘት ፡ ችለዋል ።

አንደኛውን ፡ ዋና ፡ የሥራ ፡ አርእስት ፡ የያዘው ፡ የመገናኛ ፡ መሻሻል ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝባችን ፡ ከሰጠው ፡ ጥቅም ፡ ውስጥ ፡ የአገሩን ፡ ሀብት ፡ ላገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ከማከፋፈሉ ፡ በላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ባፈራው ፡ ሰብል ፡ ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገሮች ፡ እንዲመገቡ ፡ ረድቷል ።

እናንት ፡ የዛሬ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ የነበራችሁ ፡ ሁሉ ፡ በዚያን ፡ ዘመንና ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የነበረውንና ፡ ያለውን ፡ ሁናቴ ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሳችሁ ፡ ስታስቡ ፡ በትምህርት ፡ ረገድ ፡ የነበረባችሁን ፡ ችግር ፡ ታስታውሱታላችሁ ?

ዛሬ ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ብዛት ፡ ከቀድሞው ፡ ሠላሳ ፡ አምስት ፡ ጊዜ ፡ እጥፍ ፡ ሆነዋል ።

ከጦርነት ፡ በፊት ፡ በማናቸውም ፡ ዓመት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ይማሩ ፡



የነበሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ ከ፴ ፡ አይበልጡም ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ እየተላኩ ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የሚማሩት ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

ከነዚሁም ፡ መካከል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ የመጡት ፡ ወጣቶች ፡ በመንግሥታችን ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ያገልግሎታቸውን ፡ ፍሬ ፡ ማሳየት ፡ ጀምረዋል ።

እንደምታውቁት ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የተቋቋሙት ፡ ሥራዎች ፡ እንደ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችና ፡ እንደ ሆስፒታሎች ፡ እንደ ፡ አውራጐዳናና ፡ እንደ ፡ ዓየር ፡ መንገዶችና ፡ መገናኛዎች ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ከመንግሥቱ ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ ፡ ወጪና ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ ፕላንና ፡ መቈጣጠር ፡ የሚጠይቁ ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ ከ፳፬ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በሰጠነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ የመንግሥታችን ፡ አቋቋም ፡ እርምጃቸው ፡ እየተፋጠነ ፡ ለሚጓዘው ፡ ለዛሬዎቹ ፡ ጉዳዮች ፡ እንደሚበቃ ፡ ያህል ፡ ተስማሚ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አለበት ።

በንግድ ፡ በእንዱስትሪና ፡ በገንዘብ ፡ ረገድ ፡ ከዛሬ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበረውንና ፡ ዛሬ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ ስናመዛዝነው ፡ የአዲስ ፡ ዘመናዊ ፡ ሥራዎች ፡ መቋቋም ፡ የከተማዎችንና ፡ የአውራጃዎችን ፡ መልክ ፡ ሳይቀር ፡ ለውጦት ፡ ይታያል ።

ምንም ፡ የተመኘነውን ፡ ያህል ፡ ባይሆን ፡ እንኳ ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚገባው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ካፒታል ፡ እየበዛ ፡ ስለሚሄድ ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ አዳዲስ ፡ የእርሻ ፡ ፕሮዤዎችና ፡ የማዕድን ፡ ፋብሪካዎች ፡ ይኸንን ፡ የመሳሰሉ ፡ በመኪና ፡ ኃይል ፡ የሚሠሩ ፡ ድርጅቶች ፡ ትጉህና ፡ ሥራ ፡ ወዳድ ፡ ለሆነው ፡ ሕዝባችን ፡ ሀብቱን ፡ እያፋፉለት ፡ ሄደዋል ። በዚሁ ፡ መንፈስ ፡ ከተደራጁት ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ ፡ የመስኖና ፡ የሌሎች ፡ እንዱስትሪዎችን ፡ ሥራ ፡ ለማስፋፋት ፡ የታቀደው፡ የሃይድሮ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ ፕሮግራም ፡ ተፈጽሞ ፡ ሥራው ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሊጀመር ፡ ተስፋ ፡ ተደርጓል ።

በንግድ ፡ ረገድ ፡ ስንመለከተው ፡ ከዛሬ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ተስፋ፡ ተደርጎበት ፡ ከነበረው ፡ መጠን ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሀገር ፡ ሀብቶቿን ፡ ይዛ ፡ በዓለም ፡ ገበያዎች ፡ መካከል ፡ ለመገኘት፡ ችላለች ።

ለምሳሌ ፡ ዛሬ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ በምትልከው ፡ ሸቀጥ ፡ የምታገኘው ፡ ዋጋ ፡ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ታገኘው ፡ ከነበረው ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ብልጫ ፡ አሳይቷል ።

አሁን ፡ ባለፉት ፡ ጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ በቡና ፡ ገበያ ፡ የተገኘው ፡ ትርፍ ፡ ሲታይ ፡ ከ፳፫ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ከነበረው ፡ ትርፍ ፡ በመቶ ፡ አምሳ ፡ ጊዜ ፡ በልጧል ።

በጠቅላላው ፡ የውጭ ፡ ንግድ ፡ ከቀድሞው ፡ የጨመረው ፡ በዚሁ ፡ ልክ ፡ ለመሆን ፡ የተቃረበ ፡ ነው ።

በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ወጪው ፡ ንግድ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ሚሊዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የነበረው ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ.ም. አንድ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ዘጠኝ ፡ ሚሊዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ሆኗል ።

ደግሞ ፡ በገቢው ፡ ንግድ ፡ በኩል ፡ በነዚሁ ፡ ዓመታቶች ፡ ውስጥ ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ሚሊዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ሚሊዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ደርሷል ። በጠላት ፡ ይዞታ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰው ፡ ችግርና ፡ የአገራችን ፡ ነፃነት ፡ እንደተመለሰም ፡ ያሳለፍናቸው ፡ ተከታታይ ፡ ድርቅ ፡ ዘመኖች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ቢያስከትሉም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የመንግሥታችን ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ ሁኔታ ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄዷል ። ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ የመንግሥታችን ፡ ባጀት ፡ ከአምስት ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ አይበልጥም ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ከመቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ሆኗል ።

የመገበያያ ፡ ገንዘባችንም ፡ በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ . ም . እስከ ፡ ሰማኒያ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ የነበረው ፡ ዛሬ ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ሐያ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ በልጧል ። በወርቅ ፡ የተቀመጠው ፡ ገንዘባችንም ፡ በነዚሁ ፡ ዓመቶች ፡ ውስጥ፡ ሐያ ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ብሏል ። ስለዚህ ፡ በማንኛውም ፡ ሁኔታ ፡ ስንመለከተው፡ ዛሬ ፡ እየተፋጠኑ ፡ ለሚጓዙት ፡ ለዘመኑ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ከ፳፬ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በሰጠነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተመሠረተው ፡ አቋቋም ፡ የሚበቃ ፡ መስሎ ፡ ስላልታየን ፡ እንደሚገባ ፡ ተሻሽሎ ፡ ከዘመኑ ፡ ሁኔታ ፡ ጋራ ፡ ተስማሚ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ አለበት ።

ስለንብረትና ፡ ካፒታል ፡ ጥበቃ ፡ የአገርም ፡ ውስጥ ፡ ካፒታል ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ በንግድና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ለመዋል ፡



የሚመጡትን ፡ ካፒታሎች ፡ በየዓይነቱ ፡ የሚቋቋሙትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ ለመርዳትና ፡ ለመጠበቅ ፡ ለመቈጣጠር ፡ በብርቱ ፡ አስፈላጊ ፡ እየሆነ ፡ ይህንን ፡ ለመሳሰሉ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ በየጊዜው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያወጣናቸው ፡ ሕጎች ፡ ቍጥራቸው ፡ እየበዛ ፡ እንደሄዱ ፡ ታይተዋል ። እንደዚሁ ፡ የሥራው ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ የመንግሥቱን ፡ ተቈጣጣሪነት ፡ በብዙ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚያደርገው ፡ ሆኗል ።

ይኸው ፡ ሁኔታ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶቻችንንም ፡ ቍጥር ፡ እንዲበዛ ፡ አድርጓታል ።

ለምሳሌ ፡ ባለፉት ፡ ፲፪ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በምክትል ፡ ወረዳ ፡ ከሚገኙት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በቀር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከመቶ ፡ ሰማንያ ፡ ስድስት ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ሦስት ፡ ደርሰዋል ።

የአገሪቱ ፡ በኤኮኖሚ ፡ መሻሻልና ፡ በየጊዜው ፡ እየደረጀ ፡ የሚሄደው፡ የኑሮ ፡ እድገት ፡ እንዲጠበቅና ፡ እንዲፋፋ ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆኑ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችንና ፡ የዳኞችን ፡ ቍጥር ፡ እያስጨመረ ፡ ከመሄዱ ፡ በላይ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ ኀላፊነት ፡ የተጣለባቸውን ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ እንዲስፉፉ ፡ አስገደደ ።

ለምሳሌ ፡ ከ፳፫ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የሚኒስቴር ፡ ቤቶቻችን፡ ለሚፈጽሙት ፡ ተግባር ፡ እንደ ፡ ዛሬዎቹ ፡ የሚበቁና ፡ በዘመኑ ፡ ዕውቀት ፡ የሠለጠኑ ፡ ሠራተኞች ፡ አልነበሩዋቸውም ። መሥሪያ ፡ ቤቶቻቸውም ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ በሚበቃ ፡ አኳኋን ፡ የተደራጁ ፡ አልነበሩም ።

አሁን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ገና ፡ እንደ ፡ ተመኘነው ፡ ባይሆን ፡ ከአገሪቱና ፡ ከዘመኑ ፡ የሥራ ፡ እርምጃ ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ለመራመድ ፡ በብርቱ ፡ ከሚጥሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ጋራ ፡ ከ፲፬ ፡ የማያንሱ ፡ የሚኒስቴር ፡ ቤቶች ፡ ተቋቁመዋል ።

በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ድርጅታችን ፡ በኩል ፡ ከዛሬ ፡ ፳፫ ፡ ዓመት ፡ በፊት፡ ከነበረው ፡ ሁናቴ ፡ ዛሬ ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

ምንም ፡ ወታደሮቻችን ፡ ከጥንት ፡ ጀምረው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወታደራዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ ጀግንነት ፡ ቢኖራቸው ፡ በመማሪያና ፡ በትጥቅ ፡ በዘመኑ ፡ ጦር ፡ አቅድ ፡ ሙሉ ፡ ድርጅት ፡ አልነበራቸውም ።

ዛሬ ፡ ግን ፡ ሁኔታው ፡ በጣም ፡ የተሻሻለ ፡ በመሆኑ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ የሴኩሪቴ ፡ ኰሌክቲፍ ፡ ደጋፊ ፡ በመሆኗ ፡ አጥቂዎች ፡ ለመከላከል ፡ ኮሪያ ፡ ድረስ ፡ የጦር ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ጦር ፡ ለመላክና ፡ ችሎታዋን ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ ለመግለጽ ፡ ቻለች ።

በዚህ ፡ አረማመድ ፡ ጦርን ፡ ለማደርጀት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወጪ ፡ የሚጠይቅ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀም ፡ ቢሆን ፡ ወደኋላ ፡ ሳንል ፡ በዘመናዊው ፡ አኳኋን ፡ ለማደራጀት ፡ ቈርጠናል ።

የመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ መስፋፋትና ፡ መደርጀት ፡ ያለበትን ፡ ኃላፊነት ፡ ሳይረሳ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ድርጅት ፡ እንዲመራ ፡ አስፈላጊ ፡ ስላደረገው ፡ አሁን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ክፍሎች ፡ አንዳቸውም ፡ በብቸኝነት ፡ ግዛት ፡ ተለይተው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሳይገናኙ ፡ የሚኖሩ ፡ የሉም ።

የኢትዮጵያ ፡ አውራጃዎች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ በሆነ ፡ የሥልጣኔ ፡ ጐዳና ፡ እየተከተሉ ፡ ዓላማቸውን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ለማስተባበር ፡ በሚችል ፡ በአንድ ፡ ጠቅላላ ፡ አመራር ፡ ውስጥ ፡ ተሳስረው ፡ ይገኛሉ ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ የተወደዱ ፡ ዜጎቻችን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ እኩል ፡ ወንድማማቾች ፡ ሆነው ፡ በአንድነት ፡ ለመኖር ፡ እንዲችሉ ፡ የጥንቱ ፡ አስተዳደር ፡ የግል ፡ ወይም ፡ የወገን ፡ መብት ፡ መጠቀሚያ ፡ እንዲጠፋ ፡ አድርገናል ።

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያለው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ አስተያየት ፡ በጣም ፡ እያደገ ፡ ሄዷል ።

ከ፳፫ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጨለማ ፡ ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ በአፍሪቃ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ ጫፍ ፡ የምትገኝ ፡ በብዙ ፡ የማትታወቅ ፡ አገር ፡ ነበረች ። በግፍ ፡ ለማጥቃት ፡ የተነሣባትን ፡ ጠላት ፡ በድፍረትና ፡ በጀግንነት ፡ በመከላከሏና ፡ እኛም ፡ የእንተርናሲዮናልን ፡ ሞራልና ፡ የኮሌክቲቭ ፡ ሴኩሪቴን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ለማስከበር ፡ ለዓለም ፡ በጉባኤ ፡ በገለጥነው ፡ ማስረጃ ፡ ምክንያት ፡ በበለጠ ፡ ለመታወቅና ፡ የማይጠፋውን ፡ ስም ፡ ለማግኘት ፡ ቻለች ። ዓለምም ፡ ይህ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ የሞራል ፡ ብርታትና ፡ ታላቅነት ፡ ማወቅ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ።



የተወደደች ፡ አገራችን ፡ የኢምፔሪያሊዝምን ፡ ጦርነት ፡ ብቻዋን ፡ ለመመከት ፡ በተገደደችበት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ከደረሱባት ፡ አንዳንዶችን ፡ ግፎች ፡ ለማስቀረት ፡ ተቻለ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በየብስ ፡ የተከበበች ፡ አገር ፡ መሆንዋ ፡ እንዲቀር ፡ ለማድረግ ፡ አስችሎናል ።

እላይ ፡ እንደገለጥነው ፡ በተፋጠነ ፡ እርምጃ ፡ እየተስፋፋ ፡ የሚሄደውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወጪና ፡ የገቢ ፡ ንግድ ፡ ለመርዳት ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ ያሉን ፡ ሁለቱ፡ ወደቦች ፡ ተስፋፍተው ፡ እንዲሠሩ ፡ ተቆርጧል ።

የስድሳው ፡ ዓመት ፡ በደል ፡ በመታረሙና ፡ የታመኑ ፡ ኤርትራውያን ፡ ዜጎቻችን ፡ ወደእኛ ፡ በመመለሳቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ጀምሮ ፡ የነበራትን ፡ ብሔራዊ ፡ አንድነት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለማግኘት ፡ ችላለች ።

ስለዚህ ፡ ሁሉ ፡ የሕዝባችን ፡ ቍጥር ፡ እየተባዛ ፡ በመሄዱና ፡ የወሰናችን ፡ መስፋፋት ፡ የአገራችን ፡ ሀብት ፡ እያደገ ፡ መሄድ ፡ የመንግሥቱን ፡ ኣላፊነት ፡ ሰፊ ፡ ባለ ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ መመሥረት ፡ አስፈላጊ ፡ አድርጎታል ።

ለምሳሌ ፡ ዛሬ ፡ ዋና ፡ አስፈላጊያችን ፡ ሆነው ፡ የሚገኙት ፡ እንደ ፡ ወደብ ፡ የንግድና ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ የባሕር ፡ ወሰኖች ፡ ጉዳይ ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ አልነበሩንም ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ የተማሩና ፡ የሠለጠኑ ፡ መርከበኞች ፡ ለጠረፍ ፡ ጥበቃ ፡ የሚደራጁ ፡ የባሕር ፡ መኰንኖች ፡ የወደብ ፡ ሠራተኞችና ፡ ዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ እነዚህን፡ የመሳሰሉትን ፡ የልማት ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚመለከት ፡ የያዘ ፡ ድርጅት፡ እንዲኖር ፡ አስፈለገ ።

ከነዚህም ፡ ሌላ ፡ ከባሕርና ፡ ከጠረፍ ፡ ጉዳይ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ የተሳሰሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡ ሞልተዋል ።

እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ ለመምራትና ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሥልጣኔ ፡ ረገድ ፡ የምታደርገውን ፡ ፈጣን ፡ እርምጃ ፡ ለመከተልና ፡ ከእግዚአብሔር፡ በተሰጠን ፡ ስጦታ ፡ ይበልጥ ፡ ለመጠቀም ፡ እንድንችል ፡ በትጋትና ፡ በብርታት ፡ ሁላችንም ፡ እንድንደክምበት ፡ ያስፈልጋል ።

ከወዳጅ ፡ አገሮችም ፡ እርዳታ ፡ እንድናገኝ ፡ ባለተስፋ ፡ ነን ። ባጭሩ ፡ በንግድና ፡ በእንዱስትሪ ፡ በሕዝብ ፡ ማደግና ፡ ባገር ፡ መስፋት ፡ በትምህርት ፡ በጤና ፡ ጥበቃ ፡ በእርሻና ፡ በቤት ፡ ሥራ ፡ በጠቅላላው ፡ በገንዘብ ፡ ረገድ ፡ የተደረገውን ፡ አረማመድ ፡ ስንመለከተው ፡ ከማናቸውም ፡ አገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ በ፳፭ቱ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የተደረገው ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

በየጊዜው ፡ በየቀኑ ፡ እያደገ ፡ የሚሄደው ፡ ብሔራዊ ፡ አስተያየት ፡ ኀላፊነታችንን ፡ እያበረከተው ፡ እንደሚሄድ ፡ ግድ ፡ ነው ። ይህንኑ ፡ በመሪነታችን ፡ የተጀመረውንና ፡ የሚካሄደውን ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ እንዳይቋረጥ ፡ ማድረግ ፡ ተግባራችን ፡ ነው ። ወደፊትም ፡ በበለጠ ፡ መራመድና ፡ መፈጸምም ፡ አለበት ።

በሕይወታችን ፡ ሙሉ ፡ ዋናው ፡ ዓላማችን ፡ የተወደደው ፡ ሕዝባችን ፡ ልማትና ፡ ዕድገት ፡ ሳያቋርጥ ፡ እንዲጠበቅለት ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

ለአንድ ፡ መንግሥት ፡ ማናቸውም ፡ የአስተዳደር ፡ ዓይነት ፡ ቢኖረውም ፡ በእውነቱ ፡ የዜጎቹ ፡ ደኅንነትና ፡ እድገት ፡ የሚረጋገጥበትን ፡ መንገድ ፡ በማደራጀት ፡ ከመድከምና ፡ ከመጣር ፡ በላይ ፡ የተሻለ ፡ ነገር ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም ። ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ እውነተኛ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ አይገኝም ።

አሁንም ፡ አሻሽለን ፡ በአዋጅ ፡ የምንሰጠው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለሥራ ፡ ሁሉ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚረዳው ፡ የመንግሥቱን ፡ አቋቋም ፡ በማስፋፋትና ፡ ሥልጣኑን ፡ በማዳበር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ተመሥርተው ፡ የቆዩት ፡ ሦስቱን ፡ ክፍል ፡ የመንግሥት ፡ ዘርፎች ፡ ማደርጀትና ፡ ማጠንከር ፡ ይገባናል ። እነዚህም ፡ የሕግ ፡ አውጭና ፡ የፈራጅ ፡ ያስፈጻሚ ፡ የሚባሉት ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው ።

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሚኒስትሮችና ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንቶች ፡ ሥራቸውን ፡ በሚገባ ፡ የሚፈጽሙባቸውን ፡ ሁኔታዎች ፡ ስንወስን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የኀላፊነት ፡ ሥራቸውንም ፡ በሚገባ ፡ ለመፈጸም ፡ ጭምር ፡ ለእኛና ፡ ለመንግሥቱ ፡ ተጠያቂዎች ፡ እንዲሆኑ ፡ አድርገን ፡ ነው ።

በሕግ ፡ አደራጅና ፡ አስፈጻሚ ፡ መካከል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመግባባትና ፡ የመተባበር ፡ መንፈስ ፡ እንዲኖር ፡ የማይታለፍ ፡ ግዴታ ፡ ነው ።



ሚኒስትሮቻችን ፡ በምክር ፡ ቤቶች ፡ ጥያቄ ፡ ጉዳያቸውን ፡ በምክር ፡ ቤቶች ፡ ፊት ፡ እየቀረቡ ፡ እንዲያስረዱ ፡ ወስነናል ። ይኸውም ፡ ውሳኔ ፡ ለሕግ ፡ አዘጋጅና ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ ተባብሮ ፡ ለመሥራት ፡ የሚረዳቸው ፡ ዋና ፡ መሣሪያ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

ያንድ ፡ አገር ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እያደገ ፡ ሲሄድ ፡ ሕግም ፡ እየተከታተለ ፡ በፍጥነት ፡ እየተስፋፋ ፡ የሚሄድ ፡ መሆኑን ፡ እላይ ፡ ገልጠንላችኋል ። የአዳዲስ ፡ እንዱስትሪዎች ፡ መቋቋም ፡ የአገር ፡ ሀብት ፡ ማደግ ፡ የባሕር ፡ ግዛታችን ፡ ወሰንና ፡ ወደቦች ፡ መገኘት ፡ የእንተርናሲዮናል ፡ ግዴታዎችንና ፡ ውሎችን ፡ መጠበቅ ፡ የሚያስከትል ፡ ስለሆነ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የሁለቱን ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ አላፊነት ፡ የሚያበዙና ፡ ሰፊ ፡ አስተያየት ፡ የሚጠይቁ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ሚኒስትሮቻችን ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ እየተገኙ ፡ የሚሰጧቸውን ፡ መግለጫዎች ፡ ረዳትነት ፡ ያላቸው ፡ ተግባሮች ፡ መሆናቸው ፡ የታመነ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደዘረዘርነው ፡ ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ የፈጠራቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮች ፡ የበለጠ ፡ ኀላፊነትን ፡ የሚያስከትል ፡ ስለሆነ ፡ የምክር ፡ ቤቶቹን ፡ በሁለት ፡ መንገድ ፡ ማጠንከር ፡ አስፈለገ ። በድርጅቱና ፡ በሚፈጽማቸው ፡ ተግባሮች ፡ ማለት ፡ ነው ።

በድርጅቱ ፡ ረገድ ፡ ፩ኛ ፡ የአባሎቹ ፡ ቍጥር ፡ እንዲበዛ ፡ ፪ኛ ፡ እንደራሴዎቹን ፡ በቀጥታና ፡ በምሥጢር ፡ እንዲመርጥ ፡ በመወሰን ፡ ነው ።

በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ስለምርጫ ፡ የተሰናዱትን ፡ ደንቦች ፡ ሁለቱም ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ እንዲያጠኑት ፡ ይቀርብላቸዋልና ፡ እንደተቀበሉት ፡ በፍጥነት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ወስነናል ።

የአሳባችን ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ተወላጅ ፡ ዜጎቻችን ፡ ሁሉ ፡ በመጠናቸው ፡ በምክር ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ በሚገባ ፡ እንደራሴ ፡ እንዲኖራቸውና ፡ በዘርም ፡ ሆነ ፡ በሃይማኖት ፡ በመካከላቸው ፡ አንድ ፡ ልዩነት ፡ እንዳይኖር ፡ ለማድረግ ፡ ነው ።

ማናቸውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ትክክል ፡ መብት ፡ እንዲኖረውና ፡ የተወደዱ ዜጎቻችን ፡ ሁሉ ፡ ያንድ ፡ ትልቅ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ተወላጆች ፡ ሆነው ፡ በወንድማማችነት ፡ እኩል ፡ እንዲኖሩ ፡ ዘወትር ፡ የተከተልነው ፡ ዓላማ ፡ ነው ።

የምክር ፡ ቤት ፡ አባል ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለተመረጠበት ፡ ጉዳይ ፡ ያለበትን ፡ አላፊነት ፡ አውቆ ፡ ያለፍርሃትና ፡ ያለአድልዎ ፡ ሥራውን ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲችል ፡ በሰጠነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እንደተገለጠው ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ ተከብሮ ፡ ሲሠራበት ፡ የቆየውን ፡ ልማድ ፡ በመከተል፡ ሊኖረው ፡ የሚገባውን ፡ ነጻነት ፡ ዘርዝረንለታል ።

በሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ የሚነሣውን ፡ የአሳብ ፡ ልዩነት፡ የሚወስንበትን ፡ ሁኔታ ፡ በዝርዝር ፡ ገልጠናል ። ይህንንም ፡ ስናደርግ ፡ እንደ ፡ እኛው ፡ ሁለት ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ ያሏቸው ፡ ከረጅም ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ፡ ተከብሮ ፡ የቈየ ፡ ልማዳቸውን ፡ የሚጠብቁትን ፡ የሌሎች ፡ አገር ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ አሠራር ፡ በመከተል ፡ ነው ።

የምክር ፡ ቤቶቻችን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሚበጀውን ፡ በአንድነት ፡ መንፈስ ፡ ተባብረው ፡ እንዲሠሩ ፡ እጅግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። አንደኛው ፡ ሁለተኛውን ፡ የሚቃወም ፡ መሆን ፡ የለበትም ።

በሥራ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ያልነበሩ ፡ በሕዝብ ፡ ተመርጠው ፡ የሚላኩት ፡ መማክርቶች ፡ በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በኀላፊነት ፡ የረጅም ፡ ጊዜ ፡ ልማድ ፡ ካላቸው ፡ አባሎች ፡ ዘንድ ፡ ተገቢ ፡ ምክር ፡ ለማግኘትና ፡ ለመጠቀም ፡ ይችላሉ ።

ከሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ የሚጠበቀው ፡ ውጤት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስተያየትና ፡ መሠረት ፡ ባለው ፡ መንፈስ ፡ የተጠና ፡ እንዲሆን ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

የምክር ፡ ቤቶቻችንን ፡ እንደገና ፡ አስፋፍተን ፡ ለማቋቋም ፡ ያሰብንበት ፡ ዋናው ፡ ዓላማችን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደገለጽነው ፡ የምክር፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ እየጠነከረና ፡ እየሰፋ ፡ ጠቃሚነቱም ፡ እየበዛ ፡ እንዲሄድ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ።

ሁለቱ ፡ የምክር ፡ ቤቶች ፡ ሕጎችን ፡ በማደራጀት ፡ ረገድ ፡ ከነርሱ ፡ የሚጠበቀው ፡ ነገር ፡ ታላቅ ፡ መሆኑን ፡ በማወቅ ፡ ሥራቸው ፡ የሚስፋፋበትና ፡ ሥልጣናቸው ፡ የሚበዛበት ፡ ታስቦ ፡ ተደራጅቷል ።

ሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ ባንድነት ፡ ያልተስማሙበትና ፡ የምክር ፡ ቤቶቹ ፡ በተዘጉበት ፡ ጊዜ ፡ በትእዛዝ ፡ የወጡ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ቢኖሩ ፡ ምክር ፡ ቤቶቹ ፡ በተከፈቱ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ እንዲስማሙ-



ባቸው ፡ በፍጥነት ፡ እንዲቀርቡላቸው ፡ ተወስኗል ።

ሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ ሊያስቡባቸው ፡ የሚገቡ ፡ ብዙ ፡ ሥራዎች ፡ ወደፊት ፡ ተደቅነዋል ። በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ በተለይ ፡ በገንዘብ ፡ ረገድ ፡ የሚኖራቸው ፡ ኀላፊነት ፡ በሰፊው ፡ ተዘርዝሮ ፡ ይገኛል ።

የመንግሥቱን ፡ ወጪና ፡ ገቢም ፡ ቢሆን ፡ አዲስ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ፡ ግብር ፡ ለማስከፈልም ፡ ቢሆን ፡ የሚቀርበው ፡ ማናቸውም ፡ የሕግ ፡ አሳብ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ለሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው፡ መሆኑ ፡ እንዳለበት ፡ ተገልጧል ።

ሕግ ፡ በማደራጀት ፡ ረገድ ፡ ሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ ያለባቸውን ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ አላፊነት ፡ ጠቅሰናል ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ ሸክም ፡ የሚሆን ፡ ወይም ፡ ጸንቶ ፡ የቆመውን ፡ ሕግ ፡ የሚለውጡ ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱ ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ እንዲሆን ፡ የሚጠይቁ ፡ ወይም ፡ የብድሮችና ፡ የሞኖፖል፡ ጉዳይ ፡ ያሉባቸው ፡ ወይም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ወይም ፡ ከግዛቱ ፡ ማናቸውንም ፡ ክፍል ፡ የሚለውጡ ፡ ወይም ፡ የገዥነትን ፡ ወይም ፡ የዳኝነትን ፡ ሥልጣን ፡ የሚቀንሱ ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ የሰላም ፡ ውሎችና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ ሁሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ ሆነው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋላቸው ፡ በፊት ፡ ሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ እንዲስማሙባቸው ፡ ተወስኗል ።

ስለ ፡ ሕዝብ ፡ መብቶችና ፡ ተግባሮች ፡ ከ፳ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በተሠጠው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ መብትና ፡ መሠረታዊነት ፡ የተጠቀሱ ፡ ውሳኔዎች ፡ ቢኖሩ ፡ እንኳ ፡ ዛሬ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ፡ መንግሥት ፡ የአገራችንን ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣውን ፡ ባህልና ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ድርጅቶች ፡ በመከተል ፡ ከ፳፱ ፡ በማያንሱ ፡ አንቀጾች ፡ እንደ ፡ ተወሰነው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ የሚጠቀምበትን ፡ መብት ፡ አይከለከልም ።

የሲቪል ፡ መብቶቹን ፡ ስለማግኘት ፡ ጉዳይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አይደረግም ።

በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ ሥርዓት ፡ አክብረው ፡ በነፃ ፡ ለመፈጸም ፡ አይከለከሉም።

የንግግርና ፡ የጋዜጣ ፡ ነፃነት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት፡ ሕግን ፡ ተከትሎ ፡ ተፈቅዷል ።

ስለ ፡ ደብዳቤም ፡ ፍተሻ ፡ ለአገር ፡ ጸጥታ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ አዋጅ ፡ በታወጀበት ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ማናቸውም ፡ ደብዳቤ ፡ አይፈተሽም ።

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ተከሶ ፡ ካልተመሰከረበት ፡ በቀር ፡ ወንጀለኛ ፡ ተብሎ ፡ እንዳይቈጠር ፡ በተንኮል ፡ የሰውን ፡ ሀብት ፡ ለማስቀረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በዕዳ ፡ ምክንያት ፡ ድሃ ፡ እንዳይታሠር ፡ ወስነናል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ የሚኖር ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ግፍና ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስበት ፡ በማሰብ ፡ በተደረገበት ፡ በደል ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰበትን ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ መንግሥቱን ፡ ለመክሰስ ፡ እንዲችል ፡ መብት ፡ ሰጥተነዋል ።

ምንም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ መብት ፡ ያልተሰጠ ፡ መሆኑን ፡ ብንረዳው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አገራችን ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ በመጣው ፡ ልምድ ፡ ፍርድ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የሕይወቱ ፡ ዓይነተኛ ፡ ምክንያት ፡ ስለሆነ ፡ ለእኛ ፡ በቀጥታ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ አቤቱታውን ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ማስከበር ፡ ያለባቸው ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው ። ቢሆንም ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ ድሃ ፡ ወይም ፡ ሀብታም ፡ ቢሆን ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛታችን ፡ መብቱ ፡ በትክክል ፡ እንዲጠበቅለት ፡ ለማድረግ ፡ በቅርብ ፡ የምንከታተለው ፡ ዋና ፡ ተግባራችን ፡ ነው ።

በረጅሙና ፡ በጥልቅ ፡ አስተያየት ፡ ታስቦ ፡ የተሻሻለውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለመስጠት ፡ ያሳሰበን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የቆዩት ፡ የአገር ፡ ልማዶች ፡ ሳይረሱና ፡ የሕዝባችንም ፡ የወደፊት ፡ ፍላጎት ፡ ሳይዘነጋ ፡ በተፋጠነ ፡ ዘመናዊ ፡ እርምጃ ፡ እየተስፋፋ ፡ ከሚሄደው ፡ አስተዳደር ፡ ጋራ ፡ ተዋሕደው ፡ አብረው ፡ እንዲዘልቁ ፡ ስለተመኘን ፡ ነው ።

አሳባችን ፡ ወደዚህ ፡ ሥራ ፡ ካዘነበለ ፡ ጀምሮ ፡ የነበረን ፡ ስሜት ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ምንም ፡ በጥልቅ ፡ ቢታሰብበትና ፡ ሙሉ ፡ ሆኖ ፡ ቢደራጅም ፡ ቀዋሚና ፡ መሠረታዊ ፡ ከሆኑት ፡ ከአገር ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ካልተመሠረተ ፡ በቀር ፡ ፍጻሜው ፡ ደስ ፡ የማያሰኝ ፡ መሆኑ ፡



የታወቀ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ሕዝባችን ፡ የተፈጥሮ ፡ ዝንባሌ ፡ ባለው ፡ የሕግ ፡ አስተያየት፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ብርቱ ፡ የሕግ ፡ መማሪያ ፡ ለማደራጀት ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ፈጅቶብናል ።

የመንግሥቱ ፡ ሦስተኛ ፡ ዘርፍ ፡ የሆነው ፡ የዳኝነት ፡ ጉዳይ ፡ ውሳኔዎች ፡ ሲዘጋጁ ፡ ይኸንኑ ፡ አስተያየት ፡ በመከተል ፡ ነው ።

ከሁሉ ፡ አብልጠን ፡ የምናስብበት ፡ የሕዝባችንን ፡ ደኅንነት ፡ ስለሆነ ፡ ይኸው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂዎችና ፡ ኮሚሲዮኖች ፡ ረዳትነት ፡ በትዕግሥት ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ የተጠናውና ፡ የስድስት ፡ ዓመት ፡ ድካም ፡ ያፈራውን ፡ ምርት ፡ እንድትመክሩበት ፡ በላክንላችሁ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ ከፍተኛነቱን ፡ ተረድታችሁታል ።

የመጨረሻ ፡ ፈቃዳችንን ፡ ከመስጠታችን ፡ በፊት ፡ የተሻሻለውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እንድትስማሙበት ፡ አስቀድመን ፡ ስለላክንላችሁ ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ለሕዝባችን ፡ እንደገና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ልንሰጠው ፡ ቻልን ።

በጣም ፡ የተመሰገኑት ፡ የላቲን ፡ የፈረንሳዊና ፡ የአንግሎ ፡ ሳክሶን ፡ አገሮች ፡ ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ደንቦችና ፡ ስለፖለቲካ ፡ አስተያየት ፡ በሰጡት፡ እርዳታ ፡ የተገኘው ፡ ፍሬ ፡ ለሕገ ፡ መንግሥት ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሁሉ ፡ ተስማሚ ፡ ለሆነው ፡ ለዘመናዊ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ ለወንጀል ፡ ሕግ ፡ የተመሠረተ ፡ ፍልስፍና ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ፍልስፍና ፡ ሰውን ፡ እንደተቀደሰ ፡ ፍጡር ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የሕዝባችንን ፡ የዛሬውንና ፡ የወደፊት ፡ ፍላጎቱን ፡ መሠረት በማድረግ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የቆየውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ሳንተው ፡ ከዓለም ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ የሚስማማ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ለማቋቋም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የወንጀልና ፡ የንግድ ፡ የባሕር ፡ ሕግ ፡ ጭምር ፡ የሚያደራጁ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ከሆኑት ፡ ሊቆች ፡ ቀጥረን ፡ በእኛ ፡ የዘወትር ፡ ተመልካችነት ፡ እንዲሠሩ ፡ አድርገናል ።

እነዚሁ ፡ አሁን ፡ በታላቅ ፡ ትጋትና ፡ ድካም ፡ የተጠኑትና ፡ የተደራጁት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የወንጀልና ፡ የንግድ ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ተፈጽመው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውሉና ፡ ሕዝባችን ፡ ሲጠቀምባቸው ፡

ለማየት ፡ ታላቅ ፡ ምኞታችን ፡ ነው ።

ከዛሬ ፡ ፳፬ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የሰጠነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተገቢነቱን ፡ በሚገባ ፡ እንዳስረዳ ፡ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ አሻሽለን ፡ የሰጠነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተወደዱ ፡ ዜጎቻችን ፡ እንዲጠቀሙበትና ፡ እኛም ፡ ወደ ፡ በለጠ ፡ ዕድል ፡ ልንመራቸው ፡ እንድንችል ፡ ሁሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ብርታቱን ፡ ከቸርነቱ ፡ ጋራ ፡ እንዲሰጠን ፡ ስንለምነው ፡ የ፳፭ኛውን፡ የዘውድ ፡ በዓላችንን ፡ ለማክበር ፡ ስላበቃን ፡ በጥልቅ ፡ እናመሰግነዋለን ።

ጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም.

---

# 517

የሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብ ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ እንደራሴ ፡ በክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ከበደ፡ ተሰማ ፡ አማካይነት ፡ የወከላቸው ፡ የየውራጃው ፡ አገረ ፡ ገዢዎችና ፡ ታላላቅ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በጥበባዊ ፡ ቅርጽ ፡ የተዘጋጀና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ካርታ ፡ ያለበትን ፡ ስጦታ ፡ ባቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ እንደራሴው ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

እኛ ፡ በቅርቡ ፡ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የምንገኝ ፡ ዜጎችዎ ፡ ዛሬ ፡ እግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ለመቅረብ ፡ ምክንያት ፡ የሆነን ፡

ግርማዊነትዎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆነው ፡ ካባቶችዎ ፡ ነገሥታት ፡ እስከ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የደረሰውን ፡ ተገቢ ፡ ዘውድዎን ፡ የተቀዳጁበት ፡ ፳፭ተኛው ፡ ዓመት ፡ ኢዮቤልዩ ፡ የሚከበርበት ፡ ቀን ፡ የቅርብ ፡ አገርዎ ፡ ሸዋ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስጦታ ፡ ሳይሆን ፡ ታሪክን ፡ የምታስታውስ ፡ ጠቅላላ ፡ አገርዎን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ካርታ ፡ አምሳል ፡ ስታሳይ ፡ በታላቅ ፡ ትጋትና ፡ ድካም ፡ በጠነከረ ፡ ክንድዎ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ እንዳቋቋሚት ፡ ከመላውም ፡ ዓለም ፡ ጋራ ፡ በጓደኝነት ፡ እንዳስተዋወቁአትና ፡ እንዳዛመዷት ፡ የሚነገር ፡ ነው ።



እንደዚሁም ፡ ለዚህች ፡ ለትንሺ ፡ ስጦታችን ፡ መደገፊያ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ይዋል ፡ ብለው ፡ የሚአዙበት ፡ ፩፻ ፡ ሺህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ አዘጋጅተናልና ፡ ተቀባይ ፡ እንዲታዘዝልን ፡ ባሮችዎ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ትሕትና ፡ እንለምናለን ።

ይህ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የቀረበው ፡ የመታሰቢያ ፡ በረከት፡ የግርማዊነትዎ ፡ ፍቅር ፡ አስገድዶት ፡ ፈቃዱ ፡ አዞት ፡ የቀረበ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የግዴታ ፡ ትእዛዝ ፡ ያዘጋጀው ፡ አይደለም ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ዛሬ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ያደረሰዎ ፡ አምላክ ፡ እንደዚሁም ፡ ከተወዳጁ ፡ ሕዝብዎ ፡ ሳይለይ ፡ ኀምሳኛውን ፡ ዓመት ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ለማክበር ፡ እንዲያበቃዎት ፡ ቸር ፡ አምላካችንን ፡ ባንድነት ፡ እንለምነዋለን ።

ግርማዊነትዎን ፡ ከንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቅልን ።

ኢትዮጵያ ፡ ነፃነቷ ፡ እንደተከበረ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

እግዚአብሔር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መሪነት ፡ ሲመርጠን ፡ እኛን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

በበኩላችንም ፡ እኛ ፡ ብዙዎችን ፡ መርጠናል ። ይኸው ፡ ደጃዝማች ፡ ከበደ፡ ፊትም ፡ ከንግሥት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ያሳደግነው ፡ ታማኛችን ፡ በየጊዜው ፡ ባሳየው ፡ አገልግሎት ፡ ተደስተንበታል ። እንዲሁም ፡ በቅርቡ ፡ ለሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ እንደራሴያችን ፡ ስናደርገው ፡ እናንተም ፡ በየችሎታችሁ ፡ መጠን ፡ እንደመሰለን ፡ በውስጡ ፡ በየክፍሉ ፡ ያደረግናችሁ ፡ አሳቡ ፡ የኛ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እናንተ ፡ ተባብራችሁ ፡ እንድትሠሩ ፡ በማለት ፡ ነው ።

አሁንም ፡ በመተባበር ፡ አስባችሁ ፡ ከኛም ፡ አልፎ ፡ ለትውልድ ፡ የሚቆየውን ፡ መታሰቢያ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓላችን ፡ ስለ ፡ አቀረባችሁልን ፡ እናመሰግናችኋለን ።

እኛ ፡ ለፈቀድነው ፡ ሥራ ፡ እንድናውለው ፡ ያቀረባችሁትም ፡ ገንዘብ ፡ ለኛ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የናንተንም ፡ ስም ፡ ጭምር ፡ የያዘ ፡ መታሰቢያ፡ እንዲሠራበት ፡ ተቀባይ ፡ እናዝላችኋለን ።

እናንተንም ፡ አብሮ ፡ ያድርሰን ።

* * *

ሐ) በመታሰቢያው ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ጽሑፍ ፡

ከ፲፱፻፳፫ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከፈጸሙአቸው ፡ ታሪካውያን ፡ ሥራዎች ፡ ባጭሩ ።

፩ኛ ፤ ማንም ፡ ሳይጠይቃቸው ፡ ፓርላማን ፡ አቆሙ ።

፪ኛ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ከተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ እኩል ፡ ባለወንበር ፡ እንድትሆን ፡ አደረጉ ።

፫ኛ ፤ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ በታላቅ ፡ ተጋድሎ ፡ አስገኙ ።

፬ኛ ፤ ዓለም ፡ የደረሰበትን ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲደርስበት ፡ ከኤሌሜንቴር ፡ እስከ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ዘረጉ ።

፭ኛ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጤና ፡ እንዲጠበቅ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሆስፒታሎችን ፡ አሠሩ ።

፮ኛ ፤ በሴኩሪቲ ፡ ኮሌክቲቭ ፡ የገባችበትን ፡ ውለታ ፡ ለማስፈጸም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወታደር ፡ ኮሪያ ፡ ላይ ፡ በጦር ፡ ግንባር ፡ እንዲገኝ ፡ በማድረጋቸው ፡ ኢትዮጵያን ፡ በዓለም ፡ ዘንድ ፡ ባለውሮታ ፡ አደረጓት ።

፯ኛ ፤ ከአካሏ ፡ ተነጥላ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ወድቃ ፡ የነበረችውን ፡ ኤርትራን ፡ ታምራታዊ ፡ በሆነ ፡ ታላቅ ፡ ትግል ፡ መልሰው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ቀላቀሉ ።

፰ኛ ፤ የኢትዮጵያ ፡ የመውጫውና ፡ የመግቢያዋ ፡ የሕይወት ፡ መተንፈሻ ፡ የሆኑትን ፡ የባሕር ፡ በሮችን ፡ ከፈቱ ።

፱ኛ ፤ በመንፈሳዊም ፡ በኩል ፡ ራሷን ፡ ችላ ፡ ጳጳሳትና ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትን ፡ እንድትሾም ፡ አደረጉ ።

ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ከሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡



ግዛት ፡ የቀረበ ፡ መታሰቢያ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም.

# 518

የወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ ያዘጋጀውን ፡ ግርማዊነታቸው ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ እንደሆኑ ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳየውን ፡ ከብር ፡ የተሠራ ፡ ቅርጽ ፡ ደግሞም ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ የቀለም ፡ መድና ፡ ሁለት ፡ ከወርቅ ፡ የተሠሩ ፡ የግራማን ፡ አናብስት ፡ ሥዕል ፡ ጥቅምት ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. እሑድ ፡ በልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ አማካይነት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ሲያበረክት ፡ የወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ዲሬክተር ፡ አቶ ፡ በላይ ፡ መርሻ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የአቶ ፡ በላይ ፡ መርሻ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊት ፡ እቴጌ ።

ለቸርነቱ ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ግርማዊነትዎን፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በሕይወት ፡ ስላደረሰዎ ፡ እኛ ፡ በወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የምንገኝ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አገልጋዮች ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንትና ፡ ሠራተኞች ፡ ግርማዊነትዎን ፡ እንኳን ፡ በደኅና ፡ አደረሰዎ ፡ በማለት ፡ ለበዓሉ ፡ መታሰቢያ ፡ የሚሆን ፡ ስጦታ ፡ አዘጋጅተን ፡ በተወዳጁ ፡ ልጅዎ ፡ በልዑል ፡ ጌታችን ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ አማካይነት ፤

ለግርማዊነትዎ ።

በፈረስ ፡ ላይ ፡ እንደሆኑ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ የሚያሳዩ ፡ ከብር ፡ የተሠሩ ፡ ሁለት ፡ ሐውልቶችና ፡ ከወርቅ ፡ የተሠሩ ፡ ሁለት ፡ አንበሶች ፡ ያሉበት ፡ የቀለም ፡ መድ ፡

ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡

ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ የሻይ ፡ ሰርቪስ ፡ ከነማቅረቢያው ፡ አቅርበናል ። ስጦታውን ፡ ያበረከትነው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አገልጋዮች ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡